*የመወያያ ሰነድ*
*Discussion Paper*

# ኤርትራ እንደ እናት አገር፤ ችግሮችና ፈተናዎች ትናንትም ዛሬም


ተስፋጽዮን መድሃኔ (ፕሮፌሰር)

ብረመን ዩኒቨርሲቲ፣ ጀርመን



ብረመን፣ ጀኑዋሪ፣ 2013

# ማብራሪያ እና ምስጋና

ይህ ጽሑፍ ከጥቅምት (ኦክቶበር) 5 እስከ 7፡ 2012 በጀርመን አገር፡ ካስል ከተማ፡ የኤርትራ ነፃ አውጪ የእናት አገር ግምባር ምስረታን በሚመለከት የሚካሄደውን ጉባኤ ታሳቢ በማድረግ የተዘጋጀ የምርምር ሰነድ ነው። የዚህ ጽሑፍ ዓላማ በተጠቀሰው ጉባኤ ላይ ይሁን በሌላ ጊዜና ቦታ ስለ ኤርትራ እንደ እናት አገር የሚካሄዱ ውይይቶች እንዲዳብሩ በመጠኑም ቢሆን አስተዋጽኦ ለማድረግ ነው። ስለሆነም ይህ “የመወያያ ሰነድ” ጉባኤው ከመካሄዱ በፊት አስቀድሞ እንዲሰራጭ ተደርጓል።

ይህ ጥናት እኔ በግል ተነሳሽነት ያዘጋጀሁት ነው፡፡ በስተጀርባ ሆኖ የገፋፋው ወይም ያሰማራው ድርጅት ይሁን ንቅናቄ አንድም የለም። የዚህን ጽሑፍ ይዘትም ሆነ ስርጭት በሚመለከት ሃላፊነቱ ሙሉ በሙሉ የኔ መሆኑን ለማስገንዘብ እወዳለሁ።

ይህንን ጽሑፍ ሳዘጋጅ ስማቸውን መጥቀስ የማያስፈልገኝ ወዳጆቼ በቀጥታም ሆነ በተለያዩ መንገዶች ትብብሮች አድርገውልኛል። አንዳንዶቹ ጠቃሚ ሰነዶችን በመላክ፣ አንዳንዱ ደግሞ መረጃዎችን በማቀበል፤ ሌሎችም እንዲሁ ይህ ጽሑፉ ንድፍ በነበረበት ጊዜ አስተያየታቸውን ጠይቄ፡ ጠቀሜታ ያላቸው ጥያቄዎች አቅርበዉልኛል፤ አስተያየቶችም ለግሰውልኛል።

ይህ መልዕክት በስዕለ ድምጽ፡ ማለት በአውዲዩ ቪዲዩ፡ የተቀረጸ ሲሆን በጽሑፍ ደረጃም በትግርኛ፤ በአማርኛ እና በዓረብኛ ይኸው ተሰራጭቷል፡፡ ጽሑፉ ከትግርኛ ወደ ዓረብኛና ወደ አማርኛ ሲተረጐም ለኤርትራና ለኢትዮጵያ በጎ አመለካከት ያላቸው ወዳጆቼ በተለያየ መልኩ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል፡፡

ለተባበሩኝ ሁሉ ልባዊ ምስጋና አቀርባለሁ።

ተስፋጽዮን መድሃኔ

ብረመን፣ ጀኑዋሪ፡ 2013

# *ኤርትራ እንደ እናት አገር፤*
# ችግሮችና ፈተናዎች ትናትም ዛሬም

ተስፋጽዮን መድሃኔ (ፕሮፌሰር)
ብረመን፣ ጀርመን

*ዛሬ ስለ አገር-ቤት ወሬ ለመስማት የሚጓጓ ኤርትራዊ ቁጥሩ አነስተኛ ነው፣ ወይም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየመነመነ መጥቷል። ኤርትራን አስመልክቶ የሚተላለፉት ዜናዎች የሚያሳዝኑና የሚዘገንኑ ብቻ ናቸው። በታወቁ ዓለም አቀፍ የዜና አውታሮች ሳይቀር በሚተላለፉ ዜናዎች፡ ሁሌም ማለት ይቻላል፡ አገሪቱ ከውድቀት፡ ከመከራና ከስቃይ ጋር በተያያዙ ርዕሶች ብቻ ነው የምትጠቀሰው። በዚህ ሁኔታ ላለችው ኤርትራ እርካታና እፎይታ የሚባሉ ፅንሰ-ሃሳቦች ባዕድ ሆነዋል።*

*ሕዝባችን ሊገመት በማይቻል የከፋ የመከራ ህይወት ውስጥ እንዳለ እውነተኛ የሆነ ታዛቢ ሁሉ የሚመሰክረው ሃቅ ነው። መላ ሕብረተሰባችን በማንኛውንም የህይወት ገጽታዎች በታሪከ ታይቶ በማይታወቅ መጠን እየተጨቆነ፡ እየተሰቃየና እየተረገጠ ይገኛል። ኤርትራ አጣዳፊ ዕርዳታ እየጠየቀች ነው። ህዝብዋ በእናት-አገር ግምባር መልክ ተደራጅቶ ህልውናዋን ያድን ዘንድ አብቱታዋን እያቀረበች ነው።*

*ይህ ሁኔታ ስለ ኤርትራ እንደ እናት አገር እንድንመራመርና እንድንወያይ እየጋበዘን ብቻ ሳይሆን በአጽንኦት "እየገዘተን" ነው"። እኔም ለዚሁ ጥሪ መልስ በአቅሜ ይህንን "ኤርትራ እንደ እናት አገር፤ ችግሮችና ፈተናዎች ትናትም ዛሬም" የተሰኘ ሰነድ ለውይይት ይረዳ ዘንድ እነሆ አሰራጫለሁ፡፡*

*መልዕክቴን ማስተላለፍ ከመጀመሬ በፊት ግን የኢትዮጵያ መንግሥት መሪ የነበረው የአቶ መለስ ዜናዊን ሕለፈተ-ህይወት በሚመለከት አጠር ያለ መልዕክት ማስተላለፍ አስፈላጊ ይመስለኛል።*

*ሰሞኑን የአፍሪካ ቀንድ ፖለቲካን የሚከታተሉ ታዛቢዎች የአቶ መለስን ዕረፍት አስመልክቶ ግምገማ እና ምስክርነት እየሰጡ ያሉበት ወቅት ነው። ኢትዮጵያዊያን እና ኤርትራዊያን ብቻ ሳይሆኑ የታወቁ የውጭ አገር ተንታኞችና መሪዎችም የተሰማቸውን ሀዘን፡ የመራራነቱ መጠን በሚለያይ ቋንቋ፡ ሲገልጹ ሰንብተዋል።*

*በዚህ አጋጣሚ እኔም ባንዳንድ አቶ መለስ ሲከተላቸው በነበሩት የፖለቲካ ዓላማዎችና ሲያካሂዳቸው በነበሩት እንቅስቃሴዎች ላይ የነበሩኝ ያለመርካትና ነቀፌታዎች እንደተጠበቁ ሆነው፡ ወጣት በሚያስብል ዕድሜው ከዚህ ዓለም በመለየቱ የተሰማኝን ሐዘን ለመግለጽ እሻለሁ። ለቤተሰቡና ለወገኖቹም እንዲሁ ጽናቱን እመኝላቸዋለሁ።*

*አቶ መለስ በወጣትነት ዕድሜው በመቀጨቱ ያዘንኩበት የተለያዩ ምክንያቶች አሉኝ። ከምክንያቶቹ አንዱ የሚከተለው ነው፡፡ አቶ መለስ ኤርትራን በሚመለከት የተከተለው ፖሊሲና ያስከተለው ውጤት አከራካሪ ነው። አሁን ይህንን አስመልክቶ እዚህ ውስጥ*

ዝርዝር ትንተና ልገባ አልፈልግም። ለኤርትራ ተቆርቋሪ በመምሰል በተግባር ግን ጐጂ የሆኑ እርምጃዎች ሲፈጽም እንደነበር ግልጽ ነው። ሆኖም ግን፡ ቂም ባልይዝበትም ድርጊቱን ልረሳው አልችልም። ረዥም ዕድሜና ጤና ሰጥቶት ቢቆይ ኖሮ፡ ከጥቂት ዓመታት በሁዋላ፡ ሰፋ ያል ተሞክሮና የላቀ ብስለት አግኝቶ፡ ሁላችንም ማድረግ እንደሚገባን፡ ያለፈው አካሄዱን መልሶ በመመርመር ተምሮ፡ ከበደላቸው ክፍሎች ጋር መረዳዳት ምናልባት ይችል ነበር ብዬ እገምታለሁ። ይህን ለማድረግ ዕድል ባለማግኘቱ በጣም አዝናለሁ።

አቶ መለስ አከራካሪ የሆኑ ቅርሶች ለውርስ ትቶ አልፈዋል። አንዳንዶቹ እያሞጐሱትና እየመረቁት ናቸው፣ ሌሎች ደግሞ እየወቀሱትና እየረገሙት ናቸው። ብዙ ጊዜ መሪዎች በሞት ሲለዩ ስለነሱ የሚሰጡት ሚዛኖች የተለያዩ ናቸው። የአንዳንዱ ወደ አዎንታ፡ ያንዳንዱ ደግሞ ወደ አሉታ ያደላ ይሆናል። ይህ እውነት ነው። ሆኖም አቶ መለስን በሚመለከት ያለው ያስተያየት ልዩነት በጣም ሰፊና ጥብቅ ወይም ስለታም በመሆኑ፡ አስገራሚ ባይሆንም፡ ጠለቅ ያለ ትርጉም ያለው ነው።

በተቃዋሚ ካምፕ ያሉ ኤርትራውያንም ለሚቹ ከፍተኛ ምስጋና የተላበሱ አስተያየቶች ሰንዝረዋል። በባህላችን ሞት ለህሊና ወይም ለስሜት የሚከብድ አጋጣሚ ነው። በዚህ ምክንያት ይመስለኛል አንድ ሰው በሞት ሲለይ በታቸለ መጠን የህይወቱን አዎንታዊ ጐኖችን ብቻ በማጉላት መሸኘት የነበረና አሁንም ያለ ባህላዊ ስነ ስርዐት ነው። ይህ እውነት ይሁን እንጂ፡ አንዳንድ ኤርትራውያን አቶ መለስን በሚመለከት ያቀረቧቸው ጽሑፎች ይዘቶች የሚስተዛዝብ ወይም የሚያስጨንቅ ገጽታዎች ነበሯቸው። በተለይም ደግሞ በአብዮታችን (ማለት በኤርትራ አብዮት) ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎችን ቸላ ብለው ወደ ጐን ያስወገዱ፡ በይዘታቸው ደግሞ ‘ከኤርትራ እናት-አገርነት’ ጋር የማይጣጣሙ የሚመስሉ መግለጫዎች ትንሽ አሳስበውኛል።

ይህንን ሁኔታ ለመታዘብ የቻልኩበት አንደ አጋጣሚ ነው። እነኚህ የኤርትራ ተቃዋሚዎች ያስተላለፏቸውን የጽሑፍ መግለጫዎች ያነበብኩት ይህንን ጽሑፍ (*‘ኤርትራ እንደ እናት አገር’ ችግሮችና ፈተናዎች ትናንትም ዛሬም)* ሳዘጋጅ በነበርኩበት ወቅት ነው። መግለጫዎቻቸው ሳነባቸው፡ ሳዘጋጀው ከነበርኩት ከዚህ ጽሑፍ ጋር የሚጋጭ ሃሳብ ያዘሉ መሆናቸውን ተገነዘብኩኝ፣ ስለዚህም ይበልጥ ሰፋ ያለ ጥናት ለማድረግ ተገደድኩ። ይህ ተያያዥ ሁኔታ ባጋጣሚ ለዚህ አርዕስት ጉዳይ በጥልቀት እንድመረምረውና በበለጠ ግልጽነት እንዳቀርበው በር ከፋች እንደሆነኝ ሳልገልጽ አላልፍም።

- ፩ -

ወደ አብዩ ርዕሳችን እንግባ። በእናት አገር መልክ የተዋቀረ፡ መድኅን የሆነ ሃይል ቶሎ እንዲደርስላት ኤርትራ ትጣራለች! የእናት አገር ግምባር አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድ ነው? እናት አገር (የትግርኛው “ዓዲ አቦ”) ሲባል፡ ይዘቱ (ትርጉሙ) ቆየት ብለን በሰፊው የምናየው ቢሆንም፡ “መሬቱ”ና ”ሕዝቡ” ብቻ ሳይሆን የህዝቡን ባህልና እሴቶች፡ ባጭሩ ስልጣኔንና ታሪክን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው። እነዚህ ሁሉ በአሁኗ ኤርትራ አደጋ ላይ ናቸው። እንዲያውም፡ በአሁኑ ሁኔታ አገሪቷ እንዳትፈርስና ሕዝቡም እንዳይጠፋ የሚያሰጋ ነው። በእንደዚህ ያለ አስጊ የታሪክ መድረክ ከተገኘን ዘንድ፤ ኤርትራ “አገሬ” ነች የሚል ሁሉ በአገር አድን ዘመቻ እንዲሰለፍ እየተጋበዘ ነው።

ኤርትራ ሦስተኛ ዓለም ተብለው ከተመደቡት አገሮች አንዷ ነች። ይህች አገር በውስጣዊ የታሪክ ሂደት የተገነባች ሳይሆን ጣሊያን ከውጭ መጥቶ ለጣጥፎ ያቆማት ሰው-ሰራሽ

አካል ናት። ከጣሊያን ቅኝ አገዛዝ በፊት ኤርትራ ለብቻዋ እንደ አንድ አካል የቆመች አልነበረችም። እንዲያውም ደጋማው ክፍል የሰሜን ኢትዮጵያ (አቢሲኒያ) አካል ነበረ። ምዕራባዊው ቆላማው ክፍልም እንደዚሁ በባህላዊ ራስ ገዝ አስተዳደር ህይወታቸው ሲመሩ የነበሩ አብዛኛው ጊዜ ከማዕከላዊና ምስራቃዊ ሱዳን ብለን ከምንጠራቸው አካባቢዎች ጋር፣ "ስናርን" ጨምሮ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሲከሰት የነበረ ግንኙነት ነበራቸው።

በ1941 የጣሊያን ቅኝ ግዛትነት ካበቃ በኋላ የታሪክ ድጋፍ አለን በማለት እንደ ኢትዮጵያ እና ግብጽ የመሳሰሉ መንግሥቶች ኤርትራ በመላ ወይንም የኤርትራ ክፍል የሆኑት አካባቢዎች እንዲሰጣቸው ጠየቁ። እንግሊዝና ኢጣሊያም እንዲሁ የየራሳቸው ጥቅምና ስትራተጂ ነበራቸው። እንግዳውስ ኤርትራ ሉዑላዊት እናት አገር ለመሆን ብቃት አላት ወይስ የላትም የሚል ፈታኝ ጥያቄ ወደ ግልጽ መድረክ ብቅ ማለት የጀመረው በዚህ ወቅት አካባቢ ነው።

የወቅቱን ሁኔታ ለመረዳት የያኔው ፖለቲካ አዝማሚያ (ሁኔታ) ማስታወስ አስፈላጊ ነው። ጣሊያን ከተሸነፈ በኋላ እንግሊዝ የቃል ኪዳን መንግስታትን በመወከል ኤርትራን ተቆጣጠረ። ረዢም ጊዜ ሳይቆይም ወታደራዊ አስተዳደሩን መሠረተ። ያ አስተዳደር እንግሊዞች የኤርትራን የወደፊት ዕድል አካባቢውን በአዲስ የቅኝ-ግዛት መልክ ለመቆጣጠር የነበራቸውን ምኞት በሚያገለግል መንገድ እንዲወሰን የሚቻለውን አደረገ።

የእንግሊዞችን ዘዴ ለመረዳት ኢትዮጵያን አስመልክቶ የጣሊያኖች የፖለቲካ መሃንዲሶች ከድሮ ጀምረው የነደፏቸውን ሁለት መመሪያዎችን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው። እነዚህ መመሪያዎችም ***"ፖለቲካ ሸዋና"*** እና ***"ፖለቲካ ትግርኛ"*** የሚባሉት ናቸው። "ፖለቲካ ሸዋና" የሚባለው በኢጣሊያ የውጭ ጉዳይ ጽ/ቤት ይበልጥኑ አትኩሮት ተሰጥቶት የተመረጠ ሲሆን፣ ይዘቱም የኢጣሊያ ጥቅም የሚጠበቀው በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት እና በኢጣሊያ አስተዳዳር ሥር በነበሩት የኢትዮጵያ አጐራባች አገሮች መካከል መልካም ግንኙነት ሲኖር ነው የሚል ነበር። ይህ እንዲፈጸም የኢጣሊያ ፖሊሲ ስልጣን "በአዲስ አበባና በሸዋ መኳንንት ዙርያ" መጠቃለል አለበት የሚል ነበር[1]።

"ፖለቲካ ትግርኛ" ግን በጣሊያን የኮሎኒ ጉዳዮች ጽ/ቤት የሚደገፍ ሆኖ የ "ፖለቲካ ሸዋና" ተጻራሪ ነበር፡፡ የዚህ መመርያ ትርጉም ወይም ይዘት ኢትዮጵያን ለመቆጣጠር የሚያገለግለው ዘዴ "የሸዋን ማዕከልነት" ለሚቃወሙ ክፍሎችን መደገፍና ማበረታታት ነው የሚል ነበር። ትግራይን በሚመለከት፣ በተለምዶ በአካባቢው ሲገዙ የነበሩት ሥልጣናቸው እንዳለ እንዲቀጥሉ እና ሃይላቸውም እንዲበራታ በማድረግ ማዕከላዊው የሸዋ መንግሥት ቁጥጥሩ እንዲላላ እና እንዲዳከም ለማድረግ ነበር *የፖለቲካ ትግርኛ* ፖሊሲ አቋም።

እንግሊዞች በኤርትራ ራስ ገዝ ወታደራዊ አስተዳዳር አቋቁመው በነበሩበት ወቅት በ1941 ዓ.ም ከጣሊያን መንግሥት ቁጥጥር ነፃ የሆነችውን ኢትዮጵያንም በአዲስ የቅኝ ግዛት መልክ ለመቆጣጠር ይሞክሩ ነበር። ይህ ዕቅድ ተግባራዊ ለማድረግ እንዲቻላቸው ከላይ ከተገለጹት ሁለት ንድፎች "ፖለቲካ ትግርኛ" የተባለችውን መርጠው መመሪያቸው አደረጓት። የኤርትራን ጉዳይም "ፖለቲካ ትግርኛ" ለሚለው ፖሊሲያቸው አመች ሆኖ በሚያገለግል መንገድ ተያያዙት።

የእንግዚዝ ወታደራዊ አስተዳዳር በኤርትራ የተከተለው መመሪያ "ፖለቲካ ትግርኛ' የምትለዋን ፖሊሲ ሲሆን፣ በዋናነት ትኩረቱ "ትግራይን ከኢትዮጵያ ነጥሎ ከኤርትራ ጋር

1. *ሃጋይ ኤርሊክ፡ ገፅ* 195

ለማዋሃድ ነበር"። ትግራይ ከኢትዮጵያ በተግባር ተነጥላ ከኤርትራ ጋር ከተዋሃደች በኋላ ሁለቱን ያጣመረ "ሃገረ-ትግራይ" የሚባል አገር ይቋቋማል። ይህ አገር በእንግሊዞች ቁጥጥር ሥር እንዲዋቀር ሆኖ ማዕከላዊነቷ ከተናጋው ኢትዮጵያ ጋር የላላ ግንኙነት ይኖረዋል፡፡ በተጓዳኙም ኤርትራንም ለመገነጣጠል የወጠነ ዕቅድ ነበር። በዚህ ዕቅድ (ፕሮጀክት) መሰረት ኤርትራ ወደ ሁለት ወይም ሶስት ልትከፋፈል ነበር፡፡ ምዕራባዊው ቆላማ አከባቢ ወደ ሱዳን እንዲጠቃለል ታስቦ ነበር፤ እዚህ ላይ መገንዘብ ያለብን በወቅቱ ሱዳን የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት መሆኗን፡ እና እንደ አስተማማኝ ደጀን ትታይ እንደነበረች ነው[2]። በተጨማሪ፡ ከምጽዋ ወደ ደቡብ በኩል ያለው የባሕር ዳር በሙሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዲጠቃለል ታቅዶ ነበር[3]። ደጋማው የኤርትራ ክፍል - እስከ ምጽዋ ያለውን አከባቢ ጨምሮ - በሙሉ ወደ ትግራይ ተጠቃልሎ ነው "ሃገረ-ትግራይ" የሚባለውን አገር ለመመሥረት ታልሞ የነበረው።

ይህንን ዕቅድ ሥራ ላይ ለማዋል የኤርትራ ወታደራዊ አስተዳደሪ የነበረው ስተፈን ሎንግሪግ" 'ትግራይ ብሔረተኝነት' (Tigrean nationalism) የሚለውን ፅንሰ-ሃሳብ በሰፊው ለማራገብ ተንቀሳቀሰ፣ በኤርትራ ፖለቲካም እንዲስተጋባ አደረገ። ይበልጥኑ ደግሞ እንግሊዞቹ የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ በሆነ በደጋማው የኤርትራ ክፍል በሚኖረው ትግርኛ ተናጋሪ የታቀደው የብሔረተኝነት ስሜት እንዲስፋፋ በከፍተኛ ጥረት ተንቀሳቀሱ[4]።

ዓላማው እንዲሳካም የኤርትራ ሕዝብ በፖለቲካ መስክ ገብቶ እርስ በእርሱ መከራከርና መነታረክ ነበረበት። ለዚህ ዓላማ ነው እንግሊዞች የፕረስ ነፃነትና የፖለቲካ ማሕበሮች በአስቸኳይ እንዲቋቋሙ ያደረጉት[5]። በእርግጥ እነዚህ ነገሮች ሁሉ ለራሳቸው ተፈላጊ ናቸው፣ ለሕብረተስብ ዕድገትም ቢሆን የሚረዱ ናቸው። ቢሆንም እንግሊዞች ይህንን ሲያቋቁሙ ለራሳቸው ጥቅም - ማለት ሕዝባችን እርስ በእርሱ እንዲባላ - መኖሩን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለብን።

የኤርትራ የፖለቲካ ሁኔታ በእንግሊዞች ሴራ ተነድፎ በነበረበት ፈታኝ ወቅት ነበር ወላጆቻችን መጪው የአገራቸውን ዕድል ለመወሰን በንቃት የተሳተፉት፡፡ ኤርትራ ምን ትሁን በሚለው ጥያቄ በአመለካከት እንደሚለያዩ አይቀሬ ነበር። ስለሆነም ተለያዩ። አንዳንንዱ ሙሉ በሙሉ ከኢትዮጵያ ጋር በአንድነት የመዋሃድ ፍላጐት ሲያስተጋቡ፡ አንዳንዶቹም ሙሉ ነፃነት የሚለውን አቋም ሲያራምዱ፡ ሌሎችም 'ፕሮተክቶረት' - ማለትም በተባበሩት መንግሥታት ወይንም በእንግሊዝ ጥበቃና ቁጥጥር ሥር - ይሻላል ሲሉ ነበር። ኤርትራን ከፋፍለህ ወደ ሱዳን እና ወደ ኢትዮጵያ ማዋሃድ የሚለው አገር የሚያጠፋ ሃሳብ በተግባር እንዲውልም ቀያሾቹ ባለ በሌለ ሃይላቸው በሰፊው ተንቀሳቀሱ።

- ፪ -

የኤርትራን ነጻነት ከሚፈልጉት የፖለቲካ ማሕበሮች መካካል አንዱ በይፋ የሚታወቅበት ስሙ „የኤርትራ ነፃነትና የዕድገት ማሕበር- ኤርትራ ለኤርትራውያን" (ምህጻረ- ስሙም "ኤርትራ ንኤርትራውያን") ሆኖ፡ እንግሊዞች ደግሞ ሊበራል ፕሮግረሲቭ ፓርቲ በማለት ሲጠሩት የነበረው ነው። ይህ ማሕበር፤ በተለይ ወደ መጀመሪያው ወቅት ኤርትራ ወደ

2. ዝኒ ከማሁ
3. ዝኒ ከማሁ ገፅ 222
4. ዝኒ ከማሁ ገፅ 225
5. ዝኒ ከማሁ ገፅ 225-226

ደቡብ ከመረብ ወንዝ ወዲያ ካሉት አገሮች (አካባቢዎች)፡ ማለትም ከትግራይ እና ከትግራይ ወዲያ ካሉት ትግርኛ ከሚናገሩ አካባቢዎች፡ ጋር ተዋህዳ ,ከእንግሊዝ ሞግዚትነት በኋላ ሉዓላዊት አገር እንደትሆን የሚል አቋም ነበረው[6]። ይህ አቋም "ትግራይ-ትግርኚ" ተብሎ የሚታወቀው መመሪያ (ፕላትፎርም) ነው።

እንግዲህ "ኤርትራ ንኤርትራውያን" የሚለው ሀረግ የ"ትግራይ-ትግርኚ" መፎክር ብቻ ነበር[7]። ታስባ፡ "ብሔረ አግአዚ" ወይም ""ምድረ አግአዚ" እየተባለች ስትጠቀስ የነበረችው አካል የምናውቃት ከመረብ ወዲያ ያለቺው አገር ሳትሆን በምስራቅ አለውሃ-ምላሽ" በምዕራብ ደግሞ "ተከዜ- ምላሽ" በመላ ያጠቃለለች ነበረች። ኋላ ግን፡ ቆየት ብለን እንደምናየው፡ በአንዳንድ አዳዲስ ክስተቶች ምክንያት ኤርትራ ለኤርትራዊያን በሚለው ማሕበር ውስጥ የአመለካከት ልዩነት በመነሳቱ "አለውሃ-ምላሽ" የሚለው አቋም (ወይም ጥያቄ) እየደበዘዘ መጣ።

የትግራይ-ትግርኚ ዓላማና ፍላጎት በመንፈሱ ምን እንደነበረ ጠለቅ ብለን ማወቅ ሊኖርብን ነው። ምናልባትም ታሪክ እራሱ እየደገመ እንዳይሆን!!

እንደ ፕሮፌሰር አለም-ሰገድ አባይ አገላለጽ፡ ትግራይ-ትግርኚ እንድ *የሪሶሪጂሜንቶ ናሺናሊዝም*፡ ማለት የማነሳሳት ወይንም በተዳከመ የማንነት መንፈስ ላይ 'ትንፋሽን የመዝራት' ብሄርተኝነት፡ ምሳሌ ወይም ዓይነት ነው[8]። *ሪሶርጂሜንቶ* በ19ኛው ክ/ዘመን ዛሬ ኢጣሊያ ተብሎ በሚታወቀው አከባቢ የተካሄደ እንቅስቃሴ ነው። እስከ 1870 ዓ.ም በዛው ወቅት የነበሩ ጣሊያንኛ የሚናገሩ አህዛብ በተለያዩ ግዛቶች ተበታትነው ሲኖሩ ነበር። *ያ ሪሶረጂሜንቶ* የተባለው እንቅስቃሴ እንግዲህ እነዚያን ተለያይተው ይኖሩ የነበሩትን ጣልያንኛ ተናጋሪዎች በሙሉ ከያሉበት አሰባስቦ "አንዲት ኢጣሊያ" የምትባል አገር ለመመስረት ሲካሄድ የነበረው የባህልና የፖለቲካ አነሳሽ እንቅስቃሴ ነው።

ኤርትራን፡ ማለት የትግራይ ትግርኚን እንቅስቃሴ፡ በሚመለከት ይህ የሚሰጠው ትርጉም ምንድ ነው? ይህ ማለት ከአክሱም ሥልጣኔ ጀምሮ ትግርኛ የሚናገር ሕዝብ የራሱ የሆነ ባህል፡ ሃይማኖትና የማንነት ስሜት የነበረውና አሁንም ያለው፡ ሲቀላቀልም የነበረና ያለም በመሆኑ አንድ አገር መሆን አለበት የሚል ነው። አለምሰገድ አባይ እንደሚለው የትግራይ-ትግርኚ መሠረታዊ እምነት "በጥንታዊነት ላይ የተመረኰዘ ሆኖ ትግርኛ ተናጋሪው ሁሉ በአንድ የፖለቲካ ጥላ ሥር"፡ ማለት በአንድ አገራዊ ክልል ውስጥ፡ የመሰባሰቡ ፍልስፍና ነበር[9]።

ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ፍጻሜ በኋላ "ፎር -ፓወር ኮሚሽን" ማለትም አራቱ ሃያላን መንግሥታት የተባሉት፡ ማለት የአሜሪካ፡ የሩሲያ፡ የፈረንሳይ እና የእንግሊዝ ተወካዮች የኤርትራን ሕዝብ ፍላጎት ለማጥናትና ለማረጋገጥ ወደ ኤርትራ በሄዱ ጊዜ "ኤርትራ ለኤርትራዊያን" ይባል የነበረው ማሕበር የማሳሰቢያ ጽሁፍ አቀረበላቸው። ባቀረበው ጽሁፍ መሰረት ትግራይ በጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ፡ በባህል፡ በታሪክና በንግድ ግንኙነት" ጥንት እንደነበረችው "የኤርትራ አካል ነች" በማለት ቀደም ብሎ "ትግራይ-ከኤርትራ ጋር

---

6. ኣለምሰገድ ተስፋይ፡ ገፅ 225
7. ኣለምሰገድ ኣባይ፣ (1997) ገፅ 325
8. ዝኒ ከማሁ(1998)፡ ገፅ 153
9. ዝኒ ከማሁ፡ ገፅ 163

ማዋሃድ" ከሚለው የእንግሊዝ ዕቅድ ጋር ሠምሮ የሚሄድ አቋም አሰማ። በማያሻማ አገላለጽ የትግራይ-ትግርኚን መሠረታዊ-እምነት እንደሚከተለው አንፀባረቀ[10]።

*"በሰሜን ኢትዮጵያ የተካሄዱ ጦርነቶች በሙሉ፤ ማለትም ጸረ- ጣሊያን፡ ግብጽ እና እንዲሁም መተማ ላይም ከድርቡሽ ጋር የተካሄደ ጦርነት በኤርትራና በትግራይ ሕዝብና መኳንንት እንጂ በሸዋዊያን አልነበረም። ይህም የሚያመላክተው፡ የዚያ ትግርኛ ተናጋሪ ሕዝብ የአካባቢ ጂኦግራፊያዊ ጐሳዊ እና ታሪካዊ ሥር-መሠረት ከሸዋ ጋር የሚያገናኝ ወይም የሚያጋራ እንደሌለው ነው። ስለ ጥንት ዘመን ስናወሳም ቢሆን የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ከኤርትራና ትግራይ (ከአክሱም) ነው የመነጨው እንጂ ከሸዋ ተነስቶ ወደ ሰሜን አልመጣም። በዛኛው ወቅት ሸዋዊያን ያልሰለጠኑ ዘላኖች (ኖማድስ) ነው የነበሩት። እንዳውም በዛው ጊዜ ሸዋ የነዚያ የትግርኛ ተናጋሪ ሕዝቦች ቀኝ ግዛት (ኮሎኒ) እንደነበረች በእርግጠኛነት መጥቀስ ይገባል"[11]።*

ይህ አባባል የሚያብራራው ነጥብ ቢኖር የኤርትራ ለኤርትራውያን መሪ ሃሳብ፡ በፕሮፌሰር ተኽስተ ነጋሽ አገላለጽ፡ "በትግራይ ሕዝብ ጥንታዊ ሞገስና ክብር፡ እና ይህ ህዝብ ከድሮ ጀምሮ በኢትዮጵያ በነበረው የልዕልና እና የመሪነት ቦታ ትዝታ ላይ የተመሰረተ መኖሩን ነው[12]።" ይህ አቋም የበላይነትን የሚያንጸባርቅ የትምክሕት መንፈስ የቃኘው እንደነበር ግልጽ ነው። በተጨማሪም የሸዋን መንግሥትነት የማይቀበል የፖለቲካ ትግርኛ ጉልህ መግለጫ ነበር።

አብሮ ከዚህ ጋር በተያያዘ መጠቀስ ያለበት አንድ ነጥብ አለ። ይኸውም "ኤርትራ ለኤርትራዊያን" ሲሉ ከነበሩት አንዳንድ አባቶች መሃል አባባላቸው የ"ኢሪደንቲዝም" - ማለት፡ በሌላ አገር (አካባቢ) አስተዳዳር ሥር የሚገኝ መሬት "የኔ ነው" ብለህ ወደ ግዛትህ የማጠቃለል - ገጽታ እንደነበረው ነው። የተፈለገው መሬትም ዛሬ በምስራቅ ሱዳን የሚገኝ፡ ከሰላንም ጨምሮ፡ ያጠቃለለ ነበር።

ከጥንት ጀምሮ ኤርትራ ወይንም ትግራይ ትግርኚን በሚመለከት በቅጡ ያላስተዋልነው አንድ አሳሳቢ ጥያቄ አለ። ይኸውም "ትግራይ -ትግርኚ" ሲባል ለነበረው ውጥን "አገር" ማን እንዲመራው ነበር የታሰበው? የሚል ነው። ለዚህም ጥያቄ መልሱ፡ ባለፉት በርካታ አመታት ልብ አላልነውም እንጂ፡ ግልጽ ነው የነበረው። ብያንስ የአብዛኛዎቹ 'የ'ኤርትራ ለኤርትራውያን' ማሕበር አባሎች ሃሳብ ያ ትግራይ-ትግርኚ የተባለው አገር በትግራይ መኳንንት (ትግሪያን አሪስቶክራሲ) ሥር እንዲመራ ነበር። ይህንን አስመልክተው አንዳንድ በወቅቱ የነበሩ የደጋማው ኤርትራ ክፍል ሊሂቃን (ኤሊቶች) የትግራይ መኳንንት ህጋውያን መሪዎቻችን ናቸው የሚል እምነት ነበራቸው። ስለሆነም ዕቅዱ ቢሳካ "ራስ ስዩም መንገሻ (የአጼ ዮሃንስ የልጅ ልጅ) የትግራይ-ትግርኚ መሪ መሆን ይችሉ ነበር የሚል ሀሳብ ነበራቸው[13]።

የትግራይ-ትግርኚ አገራዊ (ብሔራዊ) እንቅስቃሴ ከመረብ ወንዝ ባሻገር (ወዲያ)፡ ማለትም ትግራይ ውስጥ፡ የጐላ አልነበረም። በሌላ አነጋገር፡ ያ ትግራይ-ትግርኚ የሚል ሃሳብ የትግራይን ሕዝብ ቀልብ አልሳበም ነበር[14]። ነገር ግን አንዳንድ ከትግራይ መኳንንት

10. ኣለምሰገድ ኣባይ፣ (1997) ገፅ 325
11. ተኽስተ ነጋሽ በገፅ 170 ላይ እንደጠቀሰው
12. ዝኒ ከማሁ ገፅ 161
13. ኣለምሰገድ ኣባይ (1998)፡ ገጽ 43፣ እንዲሁም ሪቻርድ ገሪንፌልድ ገጽ 26
14. መድሃኔ ታደሰ፡ ገጽ 34

ውስጥ ቢያንስ ለተወሰነ ጊዜ ትግራይ-ትግርኚ የሚለውን ሃሳብ አስተናግደውት እንደነበር አንዳንድ ታዛቢዎች ይገልጻሉ። ለምሳሌ እነ ራስ ሥዩም መንገሻ እና ኃይለስላሴ ጉግሳ ትግራይ ከኢትዮጵያ እንድትገነጠል የደገፉበት ወቅት (አዝማሚያ) የነበረ ይመስላል[15]፣ ሁለቱም ባንዳንድ መድረኮች ለጊዜው በታላቋ ብሪታኒያ ወይንም በሌላ የውጭ ሃይል እንክብካቤ ሥር የሆነ የኤርትራና የትግራይ አንድነት እንዲመሠረት ፍላጐት ነበራቸው ይባላል[16]።

የትግራይ ትግርኚ አንቅስቃሴ ከትግራይ ይልቅ ኤርትራ ውስጥ የበለጠ ህላዌ ነበረው። እሱም ቢሆን በተወሰኑ የኤርትራ የደጋማው ክፍሎች ብቻ ነበር[17]፡፡ ባጠቃላይ እንግሊዞች የትግራይ ትግርኚ ስሜት በክርስትያኑ ደጋማው ክፍል ተቀባይነት እንዲኖረው ያደረጉት ሙከራ አልተሳካላቸውም። ፕሮፌሰር ሃጋይ አርሊክ እንደገለጸው እነኚያ መጠነኛ "ዘመናዊ ትምህርት" የቀሰሙ ወይንም ከተሜዎች ሆነው የነበሩ ኤርትራዊያን "ሲነሳሱት የነበረው ዘመናዊነትን በተላበሰ ሃሳብ (ወይም ራዕይ)" ነበር፡፡ ትግራይ ደግሞ የዘመናዊነት ሳይሆን፡ የኋላ ቀርነትና የወግ አጥባቂነት ተምሳሌት ሆና ትታይ ነበር። እንግዳውስ አብዛኛዎቹ የፖለቲካ መሪዎች የነበሩ ወጣት ኤርትራዊያኖች የነበራቸውን "አዲስ ፖለቲካዊ ራዕይ" ከኢትዮጵያዊነት ጋር አያያዙት፣ "አድናቆታቸውም ለኃይለስላሴ ሆነ"[18]።

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው፡ እንግሊዞቹ ራሳቸው የሚቆጣጠሩት የትግራይና የኤርትራ ውህደት ሊመሠረት ፍላጐት ነበራቸው። ቆይተው ግን በፖለቲካ ሁኔታው ለውጥ ሲከሰት፡ ይህንን ሃሳብ ትተው፡ በአሜሪካኖች የቀረበው ፌደራላዊ መፍትሔ፡ ማለትም ከኢትዮጵያ ጋር ዋስትና ያለው አንድነትን ደገፉ። አንዳንድ የኤርትራ-ለኤርትራዊያን ይባል የነበረው ማሕበር መሪዎችና የታወቁ አባላትም አቋማቸውን ለውጠው መካከለኛውን መፍትሄ - ማለት ፌደረሽንን ተቀበሉ። ይህንን ለውጥ ያደረጉትም ብርጋደር ፍራንክ ስታፌርድ የተባለው የታላቋ ብሪታኒያ ወኪል ባከሄደው "ሴራ" ከማሕበሩ ተነጥለው "የነፃነት ሕብረት ከኢትዮጵያ ጋር" (*"ናጽነታዊ ሕብረት ምስ ኢትዮጵያ"*) የሚል አዲስ ማሕበር ካቋቋሙ በኋላ ነው[19]።

ይህን 'ፌደረሽን" የተባለውን አማራጭ ሁሉም የፖለቲካ ማሕበሮች ነበር የተቀበሉት። ሲቀበሉትም ምክንያታቸው የወደዱት ምርጫቸው ሆኖ ሳይሆን፡ እነሱ እንደሚሉት ኤርትራ እንደ አንድ ወጥ አካል ሆና እንድትቀጥል አንድ እና ብቸኛው መንገድ ፌደረሽን ብቻ ስለነበረ ነው። ለምሳሌ የዚያ የነፃነት ጐራ (ኢንዲፐንደንስ ብሎክ) የተባለው ነፃነት ሲጠይቁ የነበሩት ማህበሮች ቅንጅት ፕረዚደንት፡ ራስ ተሰማ አስበሮም፡ ቀንደኛው የ"ትግራይ-ትግርኚ" ፖለቲካ አንቀሳቃሽ የነበሩ ቢሆንም፡ በተባበሩት መንግሥታት የተወሰነውን ፌደረሽን ተቀበሉት፣ እንደ ድልም ቆጠሩት። ይህ አቋም በነበረው ሁኔታ ትክክለኛነት እንዳለው ለመግለጽ የሚከተለውን አሉ። *"እኛ ..... የታገልንለት .... ሙሉ ነፃነት" እንደተመኘነው ባይሳካም፡ "ይህ የተገኘው ድል ሁላችንንም ሊጠቅመን ይገባል። ይህን ድል በመጎናጸፋችን አገራችን አልተቆራረጠችም፣ ሕዝባችንም አልተከፋፈለም'*[20]።

---

15. ሃጋይ ኤርሊክ፡ ገጽ 201፣ 202
16. ኣለምሰገድ ኣባይ (1998)፤ ገጽ 50
17. ኣለምሰገድ ተስፋይ፡ ገጽ 227-228
18. ሃጋይ ኤርሊክ፡ ገጽ 226
19. ኣለምሰገድ ተስፋይ ገጽ 425-428
20. ኣለምሰገድ ተስፋይ በገጽ 519 ላይ እንደጠቀሰው

ለነፃነት ሲታገሉ የነበሩት አባቶቻችን ፌደረሽኑን ሲቀበሉት ከውስጣዊ ስጋት ጋር እንደነበር መገመት አያዳግትም። ለምሳሌ አንጋፋው ታጋይ አቦይ ወልደአብ ወልደማርያም "ገደል ላለመግባት የእሾህ ቀጋን መታቀፍ" (ከይጸድፉ ቆንጠጢ ይሓቑፉ)"[21] የሚለውን ተረት በመጥቀስ የሁኔታውን አስቸጋሪነት ገልፀው ነበር ይባላል። አንግዲያውስ 'የኤርትራ አንድነት' ለአባቶቻችን የመጨረሻው 'ክቡር' ግብ (ስትራተጂካዊ ነገር) ነበር። ፌደረሽኑም በነሱ አመለካካት ለግባቸው መዳረሻ ዘዴ ነው የነበረው።

የአፄ ኃይለስላሴ መንግሥትም ፌደረሽኑን የተቀበለው ከልብ ረክቶበትና አምኖበት አልነበረም። አማራጭ ስላልነበረው ብቻ ነው። በወቅቱ ከኢትዮጵያ ጋር ሙሉ በሙሉ መዋሃድ ሲሉ ከነበሩ ኤርትራውያን ይልቅ በአንጻር የቆሙት ብዛት ነበራቸው። በተባበሩት መንግሥታትም የኢትዮጵያ የይገባኛል ጥያቄ በቂ ደገፍ አልነበረውም። በዚህ ምክንያትም አፄ ኃይለ ሥላሴ ፌደረሽኑን የተቀበሉት ቀስ እያሉ አፍርሰው ኤርትራን መጠቅለል እንደሚችሉ ተመክረው ስለነበረ መሆኑ ዶ/ር አማረ ተኽለ በ1964 ባዘጋጀው ሰፊ ጥናት አመልክቷል[22]።

ፌደረሽኑ በሕግ የተደነገገ የጊዜ ገደብ አልነበረውም። ሆኖም ፌደረሽኑ ለ10 አመታት ነው እየተባለ በወሬ ደረጃ እንዲስተጋባ ተደረገ። የዚያ ወሬ ስርጭት ፌደረሽኑን ለማፍረስ የሚያመቻች የስነ-አእምሮ ምንጣፍ ዘረጋ። ያንን ምንጣፍ ዘርግቶ፣ የአፄ ኃይለስላሴ መንግስት ፌደረሽኑን ቀስ በቀስ በመሸርሸር በ1962 ማለት ከ10 አመት በኋላ በአንዳንድ ኤርትራዊያን ትብብር አፈረሰው። ፌደረሽን የተባለውን ስርዓት እንደ መሸጋገሪያ ተጠቀመበት።

እንግዳውስ ለአጼ ኃይለስላሴ መንግስት ፌደረሽን ዘዴ ብቻ ነበር። ዋናው ግቡ ወይም ስትራተጂው ዞሮ ዞሮ ኤርትራን ጠቅልሎ ማስገባት ነው የነበረው።

የነበረው ፌደረሽን መሸጋገሪያ ብቻ እንደነበር ልናስታውሰውና ልናሰምርበት የሚገባ ነጥብ ነው። ለምን ቢባል ዛሬም ባለንበት አዲስ ሁኔታ ታሪክ በሆነ ነገር እየተደገመ እንዳይሆን!!

- ፫ -

በ1961 - ፌደረሽኑ በይፋ ሊፈርስ አጥቢያ - የኤርትራ አርነት ገድል (ተጋድሎ ሓርነት ኤርትራ - ተ.ሓ.ኤ)፡ በሓሚድ እድሪስ ዓወተ ወታደራዊ መሪነት የትጥቅ ትግል ይፋ አደረገ። መግለጫቸው የአገራችን የብሄርና የሃይማኖት አወቃቀር እና የቅርብ ታሪካችን ይዘት የሆነ መሰናክሎች ለኤርትራ አብዮት በትግሉ አፍላ ወቅት ችግሮች ፈጠሩበት፡፡

ኢሳያስ አፍወርቂ ከ1970 ዓ. ም. አንስቶ የራሱን ድርጅት ለመመስረት በተንቀሳቀሰበት ወቅት ከላይ የተጠቀሰው የኤርትራ ሕብረተሰብ አደረጃጀት እና በተ.ሐ.ኤ የታየውን ውስጣዊ መንገራገጭ ያለ ምንም ምሕረት መዘመዘው። ኢሳያስ "ንሕናን ዕላማናን" (እኛ እና አላማችን) በሚለው አዋጁ ሕዝብን ለማታለል ለመላ ኤርትራ "በአገራዊ የአንድነት ልሳን" አለዝቦ በተቀመረ ቋንቋ ያስተላልፍ እንጂ ሕዝበ ክርስትያን የሆነ ኤርትራዊ ሁሉ እንዲከተለው ነው ሎክ ብሎ የተማጠነው። እኛ እና አላማችን (ንሕናን ዕላማናን) የምትለዋ ሰነድ የሕዝብ ሁኔታ ያስጨነቃት ወይንም የሕዝብ መብት ጉዳይ ያሳሰባት ሰነድ አልነበረችም። ይልቁንስ ሰነድዋ ኢሳያስ ስስታም (የስልጣን) ሕልሙን ለማርካት መነሻ

21. ኣለምሰገድ ኣባይ (1998)፡ ገጽ 72
22. ኣማረ ተኽለ፡ ገጽ 353

ያደረገ ክፋት ያጠነጠነች አዋጅ ነበረች። ታጋይ ረድኢ መሓሪ ባሁኑ ወቅት ታዋቂነትን ባገኘው አዲሱ መጽሐፍ እንዳመለከተው፡ ኢሳያስ ሕዝባችንን ለማሞኘት ሲል ነው "እኛና አላማችን" (ንሕናን ዕላማናን) ያላት እንጂ አርእስተዋስ "እኔ እና አላማዬ" (አነን ዕላማይን) ነው መሆን የነበረበት[23]።

ኢሳያስ አፍወርቂ ወደ ትግሉ ሲቀላቀል እውነተኛ አላማውና ፍላጐቱ የኤርትራ ሉዓላዊ ነጻነት አልነበረም። በታላቅ ጥንቃቄ ደብቆ ሲንቀሳቀስባት የነበረችው አላማ "ትግራይ-ትግርኚ" እንደነበረች ረድኢ መሓሪ፣ ተስፋይ ተምነዎ፡ እንዲሁም ሌሎች የሕዝባዊ ግምባር ታጋዮች የነበሩ ደጋግመው ነግረውናል።

በትግሉ ወቅትም ቢሆን ኢሳያስ እና ተባባሪዎቹ ዋናው ግባቸው "ትግራይ ትግርኚ" እንደነበረ፡ ሆን ብለው ይሁን ወይንም ሳይታወቃቸው፡ በግልጽ ያመለከቱበት ጊዜ ነበር። ለምሳሌ በብሩህነቱና በጥልቅ አዋቂነቱ የሚመሰገን ረነ ሌፎርት የተባለው የፈረንሳይ ጋዜጠኛ በወቅቱ ሕዝባዊ ግምባር ተቆጣጥሮ ወታደራዊ ትግል ሲያካሂድበት ወደ ነበረው የኤርትራ በረሃ በመዝለቅ ጉብኝት ባደረገበት ጊዜ የታዘባት ነገር አለች፡፡ በ1983 ዓ. ም. ባሳተመው መጽሃፉ ከመሪዎቹ አንዱ ስለ ድርጅቱ ረዢም መግለጫ ሲያደርግ ሰማሁት ይላል። መሪው በማግለጫው "የኤርትራ ትግል ዓላማ" ምን እንደሆነ አስረድቶ ሲደመድም "እኛ የአክሱም ንጉሥነት ወራሾች ነን፣ ከዚህ የሸዋ መንግስት ጋር የሚያገናኘን አንዳችም ነገር አይኖርም!" አለ። ብልህ ታዘቢው ረነ ለፎርት እንዲህ ያለ ጀሮ የሚስብ ንግግር በቀላሉ የተሠነዘረ እንዳልሆነና ከበድ ያለ ይዘት የነበረው መሆኑን በመጽሐፉ ዘገበ[24]።

ኢሳያስ አፈወርቂ በህዝባዊ ግንባር ድርጅት ጉልበት ያዳበረው ወደ 70ኛው ግማሽ አካባቢ የአፄ ኃይለስላሴን መንግስት እና ዘውዳዊ ስርዓቱን ከነጭራሹ ኢትዮጵያ ውስጥ መንግሎ የጣለው አብዮት ከተከሰተ በኋላ ነው። በተካሄደው የኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ ደርግ ጠቅልሎ ስልጣን ያዘ፣ ብዙም ሳይቆይ የሕብረተ-ሰብአዊነትን አቅጣጫ እንከተላለን ብሎ ከሶቪየት ሕብረት ጋር ተዛመደ። ወቅቱ ቀዝቃዛ ጦርነት ተብሎ የሚታወቀው ሆኖ በሶቭየት ሕብረት በሚመራው ምስራቃዊ ጎራ እና በአሜሪካኖች ሲመራ በነበረው ምዕራባዊ ጐራ መካከል የስነ ሓሳብና ስተራተጂ ፍክክር ሲካሄድበት የነበረ ነው።

የደርግ ከምስራቃዊው ጐራ መጐዳኘት ለአሜሪካኖቹና ለምዕራባዊያን የሕሊና ዕረፍት ነሳቸው። ስለሆነም ደርግን እንዴት እንደሚጥሉት ጥናት አደረጉ። ይኸውም ንድፍ የኤርትራን አብዮት ደርግን ለመጣል መጠቀም ሆኖ፡ በሚከተለው ትንታኔ ላይ የተንተራሰ ነበር።

በትጥቅ ትግል ደርግን ሲፋለሙ ከነበሩት ንቅናቂዎች ሁሉ የጠነከረው ያ ጀብሃንና ሻዕቢያን ያቀፈ የኤርትራ አብዮት ነበር። ችግሩ፡ በአመሪካኖቹ የፖለቲካና ስትራተጂ ቀያሾች አባባል፡ የኤርትራ ድርጅቶች ዓላማ ሙሉ ነፃነት፡ ማለት ከኢትዮጵያ መገንጠል መሆኑ ነበር። ይህ ዓላማ ከአሜሪካኖቹ ስትራተጂ ጋር የሚጣጣም አይደለም፣ ምክንያቱም ኤርትራ ለብቻዋ ከሆነች ለእስራኤል ጠንቅ መሆኗን ስለማይቀር። ስለዚህም፡ የአሜሪካኖቹ ሃሳብ የኤርትራን አብዮት እንጠቀምበት፣ ስንጠቀምበት ግን የኤርትራ ነፃ መውጣት ለእስራኤል አደጋ በማይሆንበት መንገድ ወይም አኳሃን መሆን አለበት የሚል ነበር።

---

23. ረድኢ መሓሪ፣ ገጽ፡ 114
24. ረነ ለፎርት፡ ገጽ 268

የኤርትራን ጥያቄ በዚህ አገባብ ለመፍታት የተለያዩ ሃሳቦች በአሜሪካውያን ጠበብት ቀረቡ። ከነሱም አስፈላጊ የሆኑት የሚከተሉት ሁለት ሃሳቦች ናቸው፡፡

*አንደኛው ሃሳብ፡ የተ.ሓ.ህ.ት (የዛሬው ሕዝባዊ ወያኔ) መመስረት ከግምት በማስገባት፡ ትግራይ ውስጥ የመገንጠል ንቅናቄ ስላለ የኤርትራ ከኢትዮጵያ መለየት ለእስራኤል ጠንቅ አይሆንም የሚል ነበር፡፡ ትግራይ ከተገነጠለች በኋላ በሆነ መልክ ከኤርትራ ጋር መዋሃዱ የማይቀር ነው፣ የተባበረው አገር አብዛኛው ሕዝብ ደግሞ ክርስትያን ነው የሚሆነው፡፡ ክርስትያን የበዙበት የተባበረው አገር ለእስራል ጠንቅ ሊሆን አይችልም። ይህንን ሃሳብ ፕሮፌሰር ቶም ፈረር የተባለ ሊቅ ለአሜሪካ የሕግ አውጪ ሰኔት በነሐሴ 1975 አቀረበ[25]።*

*ሁለተኛው ሃሳብ ወይም እቅድ ደግሞ ጆን ስፐንሰር በተባለው ሊቅ የቀረበ ነበር። ይዘቱም የሚከተለው ነበር። ደርግን በመጣል ሶቭየቶችን ከአፍሪቃ ቀንድ ማስወጣት የሚችሉት የኤርትራ ነፃ አውጪ ድርጅቶች ናቸው፤ የነዚህ ድርጅቶች ግብ ግን ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመነጠል - ማለት ነፃነት ለማወጅ - ነው። የኤርትራ ነፃነት ግን እኛ አሜሪካዊያን የምንፈልገው ነገር አይደለም። ታዲያ ይህ ከሆነ ምን መደረግ አለበት? በሚለው ጥያቄ የሚከተለውን ዕቅድ ነድፎ አቀረበ። ይኸውም ነፃነት የሚለው አንቅስቃሴ ደርግ እስኪወድቅ ድረስ እና ሶቭየት ሕብርትም ከአፍሪቃ ቀንድ እስኪወጣ ድረስ ይቀጥል፡ ደርግ ተወግዶ ከአሜሪካ ፖሊሲ ጋር በሚጣጣም መንግሥት ሲተካ፡ ኤርትራ ነፃ ትሁን የሚል ነው።*

*የተባለው የኤርትራ ነፃነት ግን ዘላቂ ሳይሆን ላጭር ጊዜ ብቻ እንዲቀጥል ነበር ሃሳቡ። ነፃነቱ፡ በጆን ስፐንሰር አባባል **"ፍሊቲንግ ኤክስፐሪየንስ"** - ዘለቄታነት የሌለው፤ ላጭር ጊዜ ብቻ የሚኖር ተሞክሮ (ልምድ) ነው የሚሆነው። በዚህ መሠረት እንግዳውስ ኤርትራ ላጭር ጊዜ ብቻ ነው ነፃ አገር የምትሆነው ማለት ነው። ታዲያ አገሪቱ ምን ልትሆን ነው? በጆን ስፐንሰር ንድፍ ኤርትራ ሂዳ ሂዳ እንደሚከተለው ተመታትራ ትጠፋለች። ይኼውም፦ ደጋማው ክፍልና ደንካሊያ፡ እንዲሁም ከምጽዋ ወደ ደቡብ በኩል እስከ ባብ አልመንደብ ድረስ ያለው የቀይ ባሕር ደንደስ አካባቢ ወደ ኢትዮጵያ ይገባል፤ ወደ ኢትዮጵያ ገብቶ ግን የውስጥ አስተዳደር ይኖረዋል፡፡ (መገንዘብ ያለብን ከኢትዮጵያ ጋር ይዋሃዳል ሲባል አብዛኛው ከትግራይ ጋር ማለት እንደሆነ ነው፡ ምክንያቱም ኤርትራ እና ትግራይ በድምብር በቀጥታ ይገናኛሉና)። ሌላው የኤርትራ ክፍል ደግሞ -ማለት ሳሕል እና የተቀረው የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ የሆኑት የሚኖሩበት የኤርትራ ምዕራባዊ ቆላ ደግሞ ከሱዳን ጋር ይጠቃለላል። አንግዲህ ኤርትራ በእንደዚህ ያለ ንድፍ ተመታትራ ትበታተናለች። ይኼ ነበር የስፐንሰር ንድፍ[26]።*

ይህንን በሚመለከት ካሁን በፊት ደጋግሜ አንደገለጽኩት የኤሜሪካ መንግሥት የፈረርን እና የጆን ስፐንሰርን ንድፍ ግምት ውስጥ በማስገባት የፖሊሲው መሰረት ያደረገው ይመስላል።

ኤርትራ ተሰነጣጥቃ ህላዌዋ እንዲጠፋ ባነጣጠረ ረጂም የምዕራባውያን ስትራተጂ፡ ጀብሃ (ማለት ተ. ሓ. ኤ.) በህ. ግንባር (ሻዕቢያ) እና ወያኔ ጥምረት ተጠቅቶ፡ አሁን እንደሚመስለውም በራሱ በጀብሃ ውስጥ በነበሩት የሻዕቢያ አገልጋዮችና የውጭ አካላት ቅጥረኞች ተቦርቡሮና ተሰናክሎ ሰፊ አካሉ ተገፍቶ ከትግል ሜዳ ወጣ፡፡ ቀስ በቀስም የኤርትራ አብዮት በኢሳያስ ፖለቲካ መዳፍ ገባ። ስለዚህ ከ1980-81 ጀምሮ የተካሄደው

25. ዩ.ኤስ ኮንግረስ፡ ገጽ 106
26. ጆን ስፐንሰር፡ ገጽ 63-67

*ወታደራዊ ንቅናቄ "የኤርትራ አብዮት" የሚል ስያሜ ቢሰጠውም፡ ለሌላ ዓላማ - ማለት ለኢሳያስ እና ምዕራባውያን አጋሮቹ እና እንዲሁም ለሌሎች ተባባሪዎቹ ዓላማ - ነበር ያገለገለው። በሌላ አነጋገር፡ከዚያን ጊዜ አንስቶ "የኤርትራ አብዮት" በእርግጥ በህልውና ያለ ወይም እውነተኛ ነገር ሳይሆን ሕሊናን ለመጥለፍ የሚያገለግል አጭበርባሪ "ምስል (አስመሳይ)" ብቻ ነበር። ከረድኢ መሓሪ መጽሃፍ አንዲት ውብ ሃረግ ተውሼ ይህንን ዕውነታ በበለጠ ላብራራው እሞክራለሁ። "ላም ልጇ ሞታባት፤ በጥጃ ምስል ለወራት ያክል ትታለባለች"[27]፡፡ እንዲሁም የኤርትራ ወጣት አብዮቱ ተጠልፎ እያለ በአስመሳይ የኤርትራ አብዮት ለአመታት ደሙ ሲታለብ ህይወቱም ሲፈጅ ኖሯል፡፡*

*ቀደም ብሎ እንደተገለጸው የኢሳያስ ፖለቲካ በ"ትግራይ-ትግርኚ" የተመሠረተ ነበር። በስነ ሞገት አነጋገር (ሎጂክ) የትግሉ ወታደራዊ ፍልምያ ለትግራይ ትግርኚ ዓላማ በረዢሙ ያለመ እንጂ፡ ሉዓላዊነቷና አንድነቷ የተጠበቀ ኤርትራን መመስረት አልነበረም። የኤርትራ ነፃነት መፈክር ወይም ስልት ነው የነበረው፡ አሁንም ያለው።*

*አሁን ያለው የኤርትራ ሁኔታ በጣም ያሳዘነው፡ አባቱ በትግሉ ፍልምያዎች የተሰዋ፡ እርሱም ወጣት ዕድሜውን በትጥቅ ትግል ያሳለፈ፡ "ፓይሎት" በሚል የቅጽል ስሙ የሚታወቀው በፓል ቶክ ውስጥ እንዲህ ሲል የሰማሁት መሰለኝ። "እኔ የታገልኩት ለከንቱ ነበር፤ አባቴም ለብላሽ ነበር የተሰዋው!"። ይህ አባባል ንፁህና ትክክለኛ ነው። በሌላ አነጋገር፡ እሱ እያለ ያለው "እኔ ለኤርትራ ጥቅም አይደለም የታገልኩት፣ አባቴም ለኤርትራ ጥቅም አይደለም ህይወቱን የሰጠው" ነው።*

*ይህ ታጋይ እንዳለው፡ እነ ኢሳያስ ነፃነት ብለው ከሚጠሩት ሁኔታ የኤርትራ ሕዝብ አልተጠቀመም። ያ ሁሉ ህይወቱን የሰጠና አካላቱ ለጉዳት የተዳረገ ብቻ ሳይሆን፡ በትግሉ የተካፈለው ዜጋ በሙሉ ለሕዝቤና ለአገሬ ልለፍ በሚል ሕሊና ነበር። ስለዚህም ሁሉም ሱታፌ ሊከበር የሚገባ መሆኑን ላሰምርበት እሻለሁ።*

*የኤርትራ ሕዝብ አልተጠቀመም ቢባልም ያልተጠቀመ ክፍል ፈጽሞ የለም ማለት አይደለም። ሁልጊዜ ማለት ይቻላል፡ መስዋእት ይሁን ስራ ወይም አብዮታዊ ጥረት፡ 'ፍሬ-አልባ' ሆኖ አይቀርም። የሚጠቀም አካል አለ። ጥያቄው ተጠቃሚው አካል ማነው? የሚል ነው። ከኤርትራ ልጆች መስዋእት፡ ከኤርትራ ሕዝብ የገድል ስቃይ የተጠቀሙ አካላት አሉ። ደርግን ለማውደቅ እና ለሕብረተሰብአዊነት ጐራ ተደማጭነት ዕንቅፋት ለመፍጠር የተንቀሳቀሱ ምዕራባዊያን ሃይሎች ግባቸው ሰምሮላቸዋል፣ ሕዝባዊ ወያኔም ኢትዮጵያ ውስጥ የሥልጣን ወንበር መያዝ ችለዋል፣ ኢሳያስ አፈወርቂ እና ቡዱኑ ደግሞ ኤርትራ ውስጥ ነግሠው ዕቅዳቸውን እየተገበሩ ናቸው። ሌሎች አካላትም - ኤርትራውያን ግለ-ሰቦች ጨምሮ - ተጠቃሚ እንደሆኑ መገመት ይቻላል!!*

- ፬ -

*ኤርትራ በዚህ ዘመን ውስጥ በጥፋት ሂደትና በሞት ጐዳና ትገኛለች። በአገራችን ያለው መከራ ዝርዝር አስቀድሞ ተጠቅሷል። በጣም ከሚያሳዝኑትና የሚያሳስቡት ነገሮች አንዱ ያሁኑ ሁኔታ ኤርትራ ውስጥ ሊከሰት የማይገባው መኖሩን ነው።*

*ዛሬ ኤርትራ ያለው ሁኔታ ቭላዲሚር ፖዝነር የተባለ ሩስያዊ (ሶቭየት) ታዛቢ (ዘጋቢ) ወደ 80ኛው መጨረሻ ጊዜ አካባቢ የተናገረው አንድ ነገር ያስታውሰኛል። ይኼውም ፊል*

27 . ረድኢ መሓሪ፡ ገጽ 254

*ዶነሂው የተባለው አሜሪካዊ ጋዜጠኛ “ስለ አገርህ የሚያሳዝንህ ነገር ቢኖር ምንድ ነው?” ብሎ ሲጠይቀው “አገሬ የት ለመድረስ ትችል እንደነበር ግምት አለኝ፣ በእውነት ወይም በተጨባጭ የት እንዳለች ደግሞ አውቃለሁ፣ ልትደርስበት ትችል በነበረችው እና አሁን ባለችበት ሁኔታ ያለውን ሰፊ ልዩነት ሳገናዝበው ያሳዝነኛል።”* ሲል ገለጸ። ይህ አባባል የኤርትራን ሁኔታ በትክክል የሚገልጽ ነው።

ኤርትራ ምን ያህል ልትራመድ ትችል እንደነበር እናውቃለን። በተለይም እኛ የወጣትነት ጊዜያችንን ኤርትራ ውስጥ ያሳለፍን፡ ባሁኑ ጊዜ ዕድሜአችን በማምሺያው ገደማ ላይ የምንገኝ ዜጎች ሙሉ ግንዛቤ አለን!! ኤርትራዊያን በሃይለኛ ታታሪነታችን ነበር የምንታወቀው፣ እውነትም ታታሪ ነበርን፡፡ በሁኔታችንና ባለን አነስተኛ የተፈጥሮ ጸጋ ምክንያት ለመኖር ብለን እንሰራለን፡ እንጥራለን፡፡ በጎረቤት አገሮች - ለምሳሌ ኢትዮጵያ እና ሱዳን ውስጥ ስንኖር - እንደ ታታሪዎች፡ ምርታማዎች፡ ብቃት ያላቸው፡ ባለሞያዎችና ታማኞች ታውቀን ተከብረን የነበርን ነን፡፡ በእርግጥ ተፈላጊነት ነበረን፡፡

ነፃ አገር ሆነን ችሎታችንንና የአቅማችንን ክምችት ጥቅም ላይ አውለን እንደ ሕብረተ-ሰብ አብበን፡ አድገን፡ ደምቀን እና ተኳኩለን ልንታይ ነበር የሚገባው። አለመታደል ሆኖ ግን ኤርትራ ያለው ሁኔታ የዚሁ ተቃራኒ ነው!!

ኤርትራ ዛሬ በሁሉም መስፈርት አስጠሊና የተገለለች አገር ሆናለች። ሕዝባችን ባሁኗ ወቅት ደቃቃዋ የፖለቲካ መብት እንኳ የሌለው፡ ሰብአዊ መብቱ ፈጽሞ ያልተጠበቀ፡ እጅግ ከባድ ድህነት ያጎሳቌለው፡ ማህበራዊ ኑሮው ሰብአዊነት የራቀው፡ የህላዌው ሁኔታ በፍርሃትና ስጋት ተበክሎ የደህንነትና የዋስትና ጭላንጭል እንኳን የሌለው ነው፡፡ የወጣቶቹ ሁኔታ በተለይ እጅግ የሚያሳዝን የከበደ ትራጀዲ ሆኗል፡፡ ወጣቱ ሊደሰትበት በሚገባ አፍላ ዕድሜው በግድ እየታፈሰ ሳዋ ወይም አገልግሎት ለሚባለው ባርነት እየተዳረገ ነው። ወጣቶቹ ከዚያ ገሃነማዊ ሁኔታ ለማማምለጥ ሙከራ ሲያደርጉ፡ ከስደት ወደ ስደት አገር ለመሸጋገር ሲሞክሩ አንዳንዱ ባሕር ውስጥ እየሰጠሙ ለምህረት-የለሽ ዓሳ ሲሳይ እየሆኑ ነው፣ አንዳንዱ ደግሞ በአረሜኔዎች ተጠልፈው እንደ እንስሳ እየታረዱ ኩላሊታቸውና እና ሌላ ውስጣዊ አካላቸው እየተነጠቀ ሬሳቸው በሳሃራና በሲናይ ምድረ-በዳዎች እየበሰበሰ ነው፡፡ ይህ መከራ በጣም የሚዘገንን፡ ስትሰማውም እጅግ የሚያስደነግጥ ነው።

*ለመሆኑ ዜጎች ለዚህ አሰቃቂ መከራ ሲጋለጡ አስመራ ውስጥ ያለው መንግሥት ምን እየሰራ ነው? የሚል የዋህ ጠያቂ አይታጣም። አስመራ ውስጥ ያለው አምባገነን ኢሳያስ የሚመራው መንግሥት እውነትም ኤርትራዊ መንግሥት አይደለም፣ በኤርትራውያን ላይ የጥላቻና የቂም በቀል ቁርሾ በያዙ፡ ድብቅ ሴራ ባላቸው አካላት የቆመ ቡድን* (ካባል) *ነው። እነኚህ ሴረኞች በትውልድ ትግሬዎች ቢሆኑም ኤርትራዊያን ሊሆኑ የችሉ የነበሩ፡ ሆኖም ግን ምንነቱ ባልተመረመረ ችግር ምክንያት፡ ሕዝባችንን በሚያጠቃ መልኩ የ“ትግራይ-ትግርኚ” ንድፍ አዝማቾች ለመሆን የመረጡ ናቸው።*

ከዚህ ጋር በተዛመደ ሊነሳ የሚገባው አሳዛኝ ነገር አለ። ለብዙ አመታት ከበረሃ ትግል ጀምሮ እስከ ህግዲፍ መንግሥትነት ድረስ ኢሳያስን ያገለገሉ፡ እንደ እነ ሃይለ ወልደትንሳኤ፡(ድሩዕ)፡ማሕሙድ ሽሪፎ፡ እስጢፋኖስ ስዩም፡ ጴጥሮስ ሰለሞን፡ ጀርማኖ ናቲ፡ ኣስቴር ፍስሓጽዮን፡ በራኺ ገብረስላሴ፡ ዑቕበ ኣብርሃ፡ ብርሃነ ገረዝጊሄር የመሳሰሉ፡ በዛ ገሃነማዊ የዒራዒሮ እስር ቤት ውስጥ ተቆልፎባቸው አንዳንዶቹ ሞተው፤አንዳንዶቹ ደግሞ እየተሰቃዩ ሞታቸውን ይጠባበቃሉ። እነኚህ ታጋዮች የፈጸሙት ወንጀል የለም። ኤርትራ ውስጥ ዲሞክራሲ እንዲጀመር ጥገናዊ የሆነ ለውጥ በመጠየቃቸው ብቻ ነው ለዚሁ

አበሳ የተዳረጉት። እነዚህንና ሌሎች የፖለቲካ እስረኞችን የምትመለከት አንዲት አንገብጋቢ ነጥብ አለች፤ እርስዋም እኚህ በኢሳያስ የሚታሰሩና በተለያየ ዘዴ እየተገደሉ ያሉት ዜጎች በሙሉ ንጹሃን "ኤርትራዊያን" መሆናቸው ናት። በተቀረ፡ ብዙ ሰዎች እንደነገሩኝ ከሆነ፡ በትውልዳቸው ትግሬዎች የሆኑ ኤርትራውያን በኢሳያስ መንግስት እንዲገደሉ ወይንም እንዲታሰሩ የተደረጉ የሉም። ይህ አሳሳቢ የሆነ ትዝብት ነው!!

ነፃነት ተብሎ የሚጠራው ሁኔታ ከተከሰተ በኋላ ያለው ዕውነታ ኤርትራ ወደ ፊት አለመራመዷ ብቻ ሳይሆን፡ አጐራባች አገሮች በሙሉ ወደ ፊት ሲራመዱ እርስዋ ግን የኋልዮሽ እየተጓዘች ከሁሉም ጭራ ረድፍ ተሰልፋ መገኘትዋ ነው። ሌላ ቀርቶ ከነፃነት በፊት በዘመናዊ ዕደገት ኋላ ቀር የነበረችው ትግራይ እንኳን ዛሬ በድርብርብ እነሆ ኤርትራን አልፋት ሄዳለች!! ትግራይ ውስጥ ያለው ዕድገት በጣም የሚያስደሰት ነው። ትግሬዎች በእውነቱ በርትተዋል። ጥያቄው ኤርትራ እንዴት ሲሆን ነው ይህን ያህል የሰነፈችው የሚለው ነው። ያውም በትግሬዎች እየተገዛች!! ትግራይ እጅግ እያደገች፡ ኤርትራ ግን በአንጻሩ እየተዳከመች ወደ ኋሊት ስትጓዝ ማየት አስገራሚ ትዕይንት ነው።

አገራችን ከነፃነት በኋላ ምን ስለሆነች ነው በዚህ አዘቅት ውስጥ ልትገባ የቻለችው? የሚል ብዙ ወይንም አብዛኛው ኤርትራዊ የሚጨነቅበት ጥያቄ ሆኖ መጥቷል። ይህ ጥያቄ ግን ብሩህ መልስ አለበት።

ሁኔታው እንዲህ የሆነበት ምክንያት ኤርትራ ለስሙ ብቻ እንጂ በእውነት ነጻና ሉዓላዊት ስላልሆነች ነው። አንዲት አገር ነፃ ወጥታለች ሲባል፤ ነፃነቷና ሉዓላዊነቷ ነባራዊ (ወይም ዘልዓለማዊ) ነው በሚል ትርጉምና ግምት (ወይም ሃሳብ) ነው። ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ደርግ ከተወገደ በኋላ ኤርትራ ለአጭር ጊዜ ብቻ ነው ነፃና ሉዓላዊት አገር ሆና የምትቆየው። ከዚያ በኋላ ግን፡ በተጠነሰሰላት ሴራ መሰረት "ብትንትኗ" ትወጣለች። ለተወሰነ ጊዜ ሉዓላዊት አገር ተብላ በኋላ ግን እንድተበታተን በሚል ንድፍ የተቀመረ ነፃነት "እውተኛ" ነፃነት አይደለም። እንግድያውስ አሁን ኤርትራ ያለችባት ሁኔታ የነጻነትና የሉዓላዊነት ሳትሆን የመሸጋገሪያ መድረክ ነች። ያለፈው "ፈደረሽን' ወደ ፍጹም ውህደት መሸጋገሪያ መድረክ እንደነበረ ሁሉ፡ የዛሬዋ "ነፃነት" ደግሞ ለአገራችን መበታተንና ለትግራይ-ትግርኚ ምስረታ የምታመቻች መሸጋገሪያ መድረክ ናት።

አሁን የምናየው ያለን ሁኔታ የኤርትራን ህላዌ ትርጉም-አልባ የሚያደርግ ነው። ኤርትራዊ የማንነት ስሜትን የሚያዳክም፡ አገሪቱን ያለወጣቶች አስቀርቶ መጪ ዕድል እንዳይኖራት የሚያደርግ፣ ኤርትራውያን፡ በተለይ ወጣቶቹ፡ ዓይናቸውን አሁን የሚመሰገን ዕድገት ወደሚታይባት ትግራይ በቅናትና በጉጉት እንዲያተኩሩ የሚያስገድድ፤ ባጭሩ ኤርትራውያን - በተለይ ትግርኛ ተናጋሪዎች - የትግራይ-ትግርኚን፡ ዓላማ፡ ማለት ከትግራይ ጋር መዋሃድ የሚለውን ንድፍ እንዲቀበሉ በሕሊናና በስነ-ኣእምሮ የሚያዘጋጅ ነው።

የትግራይ ትግርኚ አስተሳሰብ (ሎጂክ) እንግዲያውስ ኤርትራ ሕዝቧን የማታኰራ፡ በገዛ ሕዝቧም የተጠላች እንድትሆን የሚያስገድድ ነው። የትግራይ ትግርኚ አራማጆች የነደፉትና የሚጠብቁት፡ የኤርትራ ሁኔታ እንዲህ መጥፎ ሲሆን ሕዝባችን "አሁን ትግራይ አድጋ የትና የት ደርሳ ይኼው እያየችኋት ነው" ብሎ "ከትግራይ ጋር መዋሃድ" ይሻለናል እንዲል ነው።

በደቡብም - ማለት በኢትዮጵያ በኩልም - እንዲሁ የትግራይ-ትግርኚን ንድፍ ለመተግበር ዝግጅት የሚመስል ክንዋኔ እየተፈጸመ ነበር፤ ዛሬም እየተፈጸመ ነው። የዚህ ዝግጅት ዋና

አካል ደግሞ ያች "የብሄር ብሔረሰቦች መብት እስከ መገንጠል" የምትለዋ ሰበበኛ መመሪያ ነች። ስለሆነም ሕዝባዊ ወያኔ የሚቆጣጠረው የኢህኣዲግ መንግሥት ያችን የመገንጠል መብት በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ውስጥ እንድትሰፍር አድርጓል። በአንቀጽ 39 የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት መሠረት ትግራይ ልትገነጠል ትችላለች። በእርግጥም ታዛቢዎች እንደሚሉት፡ ወያኔዎች ወይንም አንዳንድ የወያኔ አካላት ትግራይን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል እንደ መጨረሻ አማራጭ አድርገው ደብቀዋት ያሉት ካርዳቸው ነች።

ሕዝባዊ ወያኔ ይህችን የብሔሮች መብት እስከ መገንጠል የምትባለዋ ሰበበኛ ሴራ ኤርትራ ውስጥም እንድትገባ ለረዥም ጊዜ ያልተቋረጠ ጥረት አድርጓል። ዛሬም ጥረቱን እየቀጠለበት ነው። እነዚያ ከወያኔ ጋር ስትራተጂካዊ (ጥብቅ) ዝምድና አለን የሚሉ - በብዙ ታዛቢ አስተያየት ግን የወያኔ የበታች ተባባሪዎች ወይም ታዛገሮች - የሆኑት የኤርትራ (ተቃዋሚ) ድርጅቶች፡ የብሔሮች መብት እስከመገንጠል የምትለውን መመርያ መለያቸው እና አቋማቸው አድረገው እየተንቀሳቀሱባት ይገኛሉ።

ይህች የብሔሮች መብት እስከ መገንጠል የምትባል ቋንቋ በቀጥታ 'ትግራይ-ትግርኚ' ለሚለው ዓላማ የምታገለግል ነች። ብሔረሰቦቻችን፡ ወይም ከመሃላቸው አንዳንዶቹ፡ ተለይተናል ሲሉ፤ ያ ትግርኛ ተናጋሪው ደጋማው ክፍል ደግሞ ከትግራይ ጋር ይጠቃለል እና የትግራይ-ትግርኚ ሕልም እውን ይሆናል ማለት ነው።

እኔ በብሔረሰቦቻችን እኩልነት አምናለሁ። ብሔረሰቦቻችን የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን መብት እንዳላቸውም አምናለሁ፤ ይህንን ስል ግን የብሔረሰቦቻችን መብት የሚረጋገጠው በአንዲት የተዋሃደች ኤርትራ ሥር ውስጥ መሆኑን ላሰምርበት እፈልጋለሁ። የብሔሮች መብት እስከ መገንጠል የሚለውን በስመ "መብት" ተሞርኩዞ የኤርትራን አንድነት የሚያደፈርስ አጀንዳ ማካሄድ በአገር ላይ "ክሕደት" መፈጸም" (ትሪዝን) ከመሆን አያልፍም።

ቀደም ብሎ እንደተመለከተው ዛሬ ያለው ፈታኝ ውጥረት ኤርትራ ትኑር ወይስ አትኑር የሚል ነው። አገር እንድትኖር ከተፈለገ ኤርትራዊ ሁሉ ለአርነታዊ ትግል የበኩሉን ድርሻ ማወጣት ይኖርበታል። የትግሉ ዘመቻ ደግሞ በ"እናት አገር" (ግንባር ዓደ'ቦ) መልክ የተደራጀ መሆን አለበት።

- ፭ -

በተለምዶ ሲተረጐም የትግርኛው "ዓደ'ቦ" (በአማርኛ "እናት አገር") አባቶችህ፡ ከነርሱ በፊት ደግሞ አያቶችህ፡ ሲኖሩበት የነበረው አገር ወይንም አከባቢ ማለት ነው። በስነ-ፖለቲካ መስክ ግን ዓደ'ቦ ወይንም እናት አገር ጠለቅ ያለ ትርጉም ያዘለ ነው። ለአንድ የተወሰነ ወይም የታወቀ አካባቢ ወይንም ገጠር፤ ብቻ አይደለም የሚመለከት፤ የሚመለከተው ለአንድ ባለው የተለየ "ባህላዊ፤ ፖለቲካዊ፤ ማሕበራዊና ስነ ልቦናዊ" ይዘት የሚታወቅ ህዝብ ነው። በበሳል ወይም በበሰለ መልኩ ወይም ምንነቱ ከረጅም ትውልዶች አንስቶ በአንድ የተወሰነ ቦታ የሚኖር በጋራ ቋንቋ ባህልና ክብር የተሳሰረ ሕብረተ-ሰብ ማለት ነው።

የኢጣልያን አገር ለመመስረት፡ ሪሶርጂመንቶ በሚባል ንቅናቄ ከታገሉት አንዱ 'ጁዘፐ ማዚኒ' የተባለው የዓደ'ቦ (እናት አገር) ትርጉምን በሚመለከት እንዲህ አለ።

*"ዓደ'ቦ (እናት አገር) ቦታ ወይ ቦታ ብቻ ኣይደለም፤ ቦታ መሰረት ብቻ ነው፤ ዓደ'ቦ (እናት አገር) በመሰረቱ ላይ የታነጸ ሐሳብ ነው፤ የፍቅር ሐሳብ፤ የዛ ቦታ አገር ልጆች የሆኑትን ሁሉ የሚያስተባብር የውህደት መንፈስ ነው"[28]።*

በታሪክ ዓደ'ቦ (እናት አገር) የተለያየና ታዳጊ ትርጉም ነበረው፡ አሁንም አለው። ለምሳሌ አውሮፓ ውስጥ ከምእተ ዓመታት በፊት - ማለት በፊዩዳል ስርዓት ዘመን - እናት አገር ጠባብ ትርጉም ያቀፈ ሃሳብ ነበር። ሲሰጠው የነበረው ትርጉም አውራጃን፡ ክልልን፡ ክፍለ-አስተዳደርን ወይም ወረዳን የመሳሰሉት አካባቢዎችን ነበር የሚመለከት። ቆየት ብሎ ግን በአውሮፓ ውስጥ የካፒታሊዝም ስርዓት ብቅ ሲል፡ አገሩ በሙሉ ተገናኝቶና ተያይዞ በማሕበራዊና ምጣኔ ሃብታዊ ፈጣን ሂደት ግንኙነት ሲፈጥር 'እናት-አገር' የሚለው ሃሳብ የአገሩን በሙሉ ፓለቲካዊ፡ ባህላዊና ህብረተሰባዊ ማሕበረ-ሰብ የሚመለከት ትርጉም ያዘ።

ሦስተኛ ዓለም አገሮች በአመሰራረታቸውና በዕድገታቸው ደረጃ ከአውሮፓ እና ካደጉት ሌሎች አገሮች ይለያሉ። በውስጣዊ (ማለት በገዛ ራሳቸው) ታሪክ መሰረት ሳይሆን የተለያዩ ብሔረሰቦች በቅኝ ግዛት ቁጥጥር ስር በመግባታቸው ተዋቅረው የቆሙ አገሮች ናቸው። አመጣጣቸውና የዕድገታቸው ደረጃ በማያሳስብ ሁሉም እናት አገሮች ናቸው። ያ ከቅኝ ግዛትነት ነፃ ለመውጣት ያደረጉት ትግል እንደ ሕጋዊና ብቁ እናት አገርን የመከላከል አቅዋም ታውቆ በተራማጅነት እና በሰላም ሃይሎች ተደግፏል።

ከዚህ ጋር የተያያዘ ግልጽ መሆን ያለበት አንድ ነገር አለ። ወራሪዎችና አመጻኞች መንግሥታትም ቢሆኑ ለእናት አገር ዘብ መቆም ወይንም እናት አገር የሚለውን ሐረግ ለብዝበዛና ለጸረ-ሠላም ዘመቻቸው ሲሉ ይጠቅሱታል። በዚህ መልኩ የተነሳሳ የእናት አገር ግንባር ግን እውነተኛ አይደለም።፡ ይህ ሃቀኛ የሕብረተሰብ ፍቅር ያላነገበ፡ መርሆ ነው፣ የጥቂቶች የስስታምነትና የብዝበዛ ጥቅም ብቻ የሚያስጠብቅ አስመሳይ መፈክር ነው። የእናት አገር ግንባር ፍትሓዊ ሆኖ ተቀባይነት የሚኖረው ዓላማው መሠረታዊ መብቶችን ለመከላከል ወይም የሌሎችን መብት በማይጋፋ መልኩ የራስን መብት መጠቀም ሲሆን ነው።

ኤርትራ እናት አገር ነች? ወይም የኤርትራውያን እናት አገር ማን ነች? ይህ ጥያቄ በ40ዎቹ አካባቢ ብዙ ያነጋግር ነበር። አነጋጋሪ የሆነበት ምክንያትም 'ኤርትራ ለኤርትራዊያን' የሚባል ማሕበር ሲያራምደው የነበረው 'የትግራይ-ትግርኚ' ፖለቲካ ነው። በፊት እንዳብራራሁት፤ የዚያ ማሕበር አባላት 'ኤርትራ' ሲሉ፡ በተለይ ወደ መጀመሪያው አካባቢ፡ "ትግራይ ትግርኚ" (አለውሃ ምላሽ) ማለታቸው ነበር። ስለሆነም "እናት አገራችን "(ዓደ'ቦ) ሲሉ በተግባር "ትግራይ ትግርኚ" ይሉ ነበር ማለት ነው።

ዛሬስ ትግርኛ ተናጋሪ የሆነው ኤርትራዊ "እናት አገሬ" ሲል ምን ወይም የትኛዋን አገር ማለቱ ነው? ትግሬዎችሳ ማንን ወይንም የትኛዋን አገር ነው እናት አገራችን የሚሉዋት?[29]

---

28. *ማውሪዚዮ ቪሮሊ፤ በገጽ 84-85 ላይ እንደጠቀሰው*
29. በእነዚህ ገፆች ውስጥ ያሉት የኤርትራ እናት-አገርነትን፡ እንዲሁም ትግራይንና እናት-አገርነትን በሚመለከት የቀረቡ የጥያቄና መልስ ተጨባጭ መረጃዎች አብዛኛዎቹ - ወይንም ሁሉም ማለት ይቻላል - አለምሰገድ አባይ ከጻፈው "Identity Jilted or Re-imgining Identity" የሚል መጽሓፍ የተገኙ ናቸው። ፕሮፌሰር ኣለምሰገድ እንደዚህ ያለ በመረጃ የደለበ መጽሐፍ በማበርከቱ ላመሰግነው እፈልጋለሁ። እርግጥ አንዳንድ የማልስማማባቸው ነጥቦች ቢኖሩም መጽሐፉ ጠቃሚ መሆኑን ሳልገልጽ አላላፍም።

እናት-አገር (ዓደ'ቦ) የሚለውን ቃል ትግርኛ ተናጋሪ ኤርትራዊያን በአንድ ዓይነት አይረዱትም። ለምሳሌ በደጋማው ኤርትራ ስንመለከት፡ በተራው (ሲቪል) ሕዝብና በፖለቲካ ተዋንያን መካከል የሃሳብ (ወይም የአተረጓጎም) ልዩነት አለ። የተራው ሕዝብ የማንነት ስሜት ወይም እምነት ጥንት በቆየው ታሪክ፡ ልማድና ዝምድና ላይ የተመሰረተ ነው። ከዚህ ጋር በተያያዘ መገንዘብ ያለብን አንድ ነጥብ አለ፤ ኤርትራ በጣልያን ሥር በነበረችበት ወቅትም ቢሆን፡ ይህ የደጋማው ክፍል ሕዝብና ከመረብ ወንዝ ማዶ የሚገኘው የትግራይ ሕብረተሰብ እንደጥንቱ እየተገናኘና እየተጋባም መኖሩ ነው።

እናት አገራችን (ዓደ'ቦና) ማነች ትላላችሁ? ሲል አለምሰገድ አባይ በኤርትራ ደጋማው ክፍል ላሉት ተራ ሕዝብ መጠይቅ (ኩወሽነር) አቅርቦላቸው ነበር። ከተጠየቁት ተራ ሕዝብ 21.4% ብቻ ነበሩ እናት አገራችን (ዓደ'ቦና) ኤርትራ ነች ብለው ያሉት። አብዛኛዎቹ፡ (ማለት 53.6%) እናት አገር (ዓደ'ቦና) የሚሏት መንደራቸውን ወይንም አባቶቻቸው እና አያቶቻቸው የተወለዱበት አካባቢን ነው። ከነዚህም በጣም ጥቂቶች አገራችን (ዓደ'ቦና) ትግራይ-ትግርኚ ወይንም ትግራይ ነች ያሉም ነበሩባቸው[30]፡፡

ተራው (ሲቪል) የትግራይ ሕዝብሳ? አብዛኛዎቹ ሳይሆኑ በርከት ያሉ (39.3%) የትግራይ ሲቪል ሰዎችም እናት አገራችን (ዓደቦና) ብለው የሚሏት መንደራቸውን ወይንም የተወሰነ የትውልዳቸው አከባቢን ነው። ወደ 25% ግን እናት አገራችን ትግራይ ነች ብለዋል።

ኤርትራውያንና ትግሬዎች በጣሊያን አገዛዝ ምክንያት ለ62 ዓመታት ተለያይተው ኖረዋል። ይህ መለያየት ባስከተለው ሰበብ ምክንያት ታሪካዊ ጠላታችሁ ማን ነው ወይንም ታሪካዊ ጠላቶቻችሁ እነ ማን ናቸው? በሚለው ጥያቄ ይለያያሉ። ኤርትራውያኖች በነዚያ 62 ዓመታት ውስጥ በጣልያን እንደ ባሮች ይገዙ ነበር። ትግሬዎች ደግሞ የአፄ ዮሃንስ ሥልጣነ-ንግሥና ተነጥቀው በሸዋ አማራዎች ይገዙ ነበር። ኤርትራውያን ጣልያኖችን እና ሌሎችን የባሕር ማዶ ባዕድ ገዢዎች ጠሉ። ትግሬዎቹ ደግሞ በአማራዎች ላይ - በተለይ ደግሞ በሸዋ አማራዎች ላይ - ቂም እና ቅራኔ አሳደሩ።

ከዚህ ታሪክ የመነጨ ይመስለኛል፡'ታሪካዊ ጠላቶቻችሁ እነማን ነቸው?' ለሚለው ጥያቄ ኤርትራዊያን እና ትግሬዎች የተለያዩ መልሶች አሏቸው። ከእነኚያ ተራ (ሲቪል) ኤርትራውያን አብዛኛዎቹ (86%) ታሪካዊ ጠላቶቻቻን ብለው የጠቀሱዋቸው፡ መጀመሪያ ቱርክን፡ ቀጥሎ ደግሞ በቅደም-ተከተል ግብፅ፤ ጣሊያንና እንግሊዝን ጠቅሰዋል። በመጨረሻ ያስቀመጧቸው ኃይለስላሴን እና ደርግን ነበር። ትግሬዎቹ ግን ታሪካዊ ጠላቶቻችሁ እነ ማን ናቸው ሲባሉ አብዛኛዎቹ (ማለት 82.1%) "አማራዎች፤ በተለይ የሸዋ አማራዎች" ብለው ነበር የመለሱት። አነስተኛ ቀጥር (ማለት 10.7% ብቻ) ቱርክንና ጣልያንን እንደ ታሪካዊ ጠላቶች ጨመሯቸው።([31])

የኤርትራና የትግራይ ልሂቃን (*ኤሊት) -* ማለትም የፖለቲካ ተዋንያን - እናት አገራችሁ ማነች? ተብለው ሲጠየቁ በሰጡዋቸው መልሶች ልዩነቶች ነበሩ። የሰጡዋቸው መልሶች ምን ነበሩ? በኤርትራውያኖች እንጀምር። በኤርትራውያን ፖለቲከኞች መሃልም ቢሆን እናት አገራችን ማን ነች በሚለው ጥያቄ ላይ እዚህ ግባ የማይባል ትንሽ ልዩነት ነበር። ከተጠየቁት አነስተኞቹ ክፍል (ማለት 26.5%) እናት አገር ብለው የሚጠሩት እነሱ ወይንም አባቶቻቸው የተወለዱበት ቦታ መሆኑን ገለጹ። አብዛኛዎቹ ግን (ማለት 71.4%)

30. ኣለምሰገድ ኣባይ (1998)፡ ገጽ 160
31. ዝኺ ከማሁ፡ ገጽ 153-154

እናት አገራችን ኤርትራ ነች ነበር ያሉት። ለምሳሌ አምባሳደር ኣድሓኖም ገብረማርያም እንደሚከተለው ብሏል።

> *"ለነፃነት በተደረገው ትግል ተሰልፎ ሲታገል የነበረ ማንኛውም ታጋይ ሁሉ ወንድሜ ነው። መሐመድ ያስማንም (ታጋይ የነበረ) ወንድሜ ነው። ለሁሉታችን ደግሞ እናት አገር ሲባል ቀድማ ወደ ሕሊናችን የምትመጣው ኤርትራ ነች"[32].*

እናት አገሬ 'ትግራይ-ትግርኚ' ነች ብሎ የመለሰ በጥያቄው የተሳተፈ ኤርትራዊ የፖለቲካ ተዋናይ የለም።

ኤርትራውያን እናት አገራችን ኤርትራ ናት ሲሉ ግን፡ ይህች ኤርትራ እናት አገር ከሆነች ረዢም ዘመን እንዳላስቆጠረ ያምናሉ። እንዲያውም ኤርትራዊ ብሂርተኝነት ራሱ የተነሳው ወይም የተጀመረው በጣሊያኖች የቅኝግዛትነት መነሻ - ማለት በ19 ክፍለ-ዘመን መጨረሻ እንደነበር ያሰምሩበታል። ይህ ማለት ደግሞ፡ ቆየት ብየ እንደምገልጸው፡ የኤርትራ እናት-አገርነት በዕድገት ሂደት ያለ ነው ማለት ነው።

በጥያቄው የተሳተፉት የዛሬው የትግራይ ፖለቲከኞች (ወይም የፖለቲካ ተዋንያን - ማለት ኤሊት) እናት አገራችሁ ማነች ለሚለው ጥያቄ የሰጡት መልስ በመንፈስም በአስተሳሰብም ኤርትራውያን ፖለቲከኞቹ ከሰጡት መልስ አሳሳቢ በሆነ መጠን ይለያል። ከተሳተፉት የትግራይ ፖለቲከኞች መሃል እናት አገራችን ኢትዮጵያ ነች ብለው የመለሱ 3.6% ብቻ ናቸው። አብዛኛዎቹ በጥያቄው የተሳተፉ የትግራይ ፖለቲከኞች ግን እናት አገራችን ትግራይ ነች ነበር ያሉት። ኢትዮጵያ አላሉም። አቶ ስብሓት ነጋ ይህንን ጥያቄ ሲመልስ፡ ላንዳፍታ "ዝግ ካለና ካመነታ በኋላ"፡ እናት አገር ሲባል በአእምሮው ውስጥ ድቅን የምትልበት "ትግራይ" መሆኗን ገልጿል። እንደዚሁም አቶ ጸጋይ በርሄ - እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የትግራይ ክልል ፕረዚደንት የነበረና፡ ዛሬ ግን የሕዝባዊ ወያነ ማዕከላዊ ኮሚቴ ስራ አስፈጻሚ አባል የሆነው - ይህ ጥያቄ ቀርቦለት ሲመልስ ሳያመነታ በቀጥታ "እናት አገሬ ትግራይ ነች" ነው ያለው። ኢትዮጵያ ነች አላለም። "ብትግሬነቴ በኩል አድርጌ ነው ኢትዮጵያዊ የምሆነው" በማለት ግን መልሷን ስስ በሆነች ኢትዮጵያዊነት ሸፋፍኗታል።[33]

ይህ እናት አገራችን ትግራይ እንጂ ኢትዮጵያ አይደለችም የሚል መልስ ከታወቁ የሕዝባዊ ወያኔ አመራር አካሎች ሲደመጥ የሚያሳስብ ክስተት ነው። (ለምሳሌ አንድ በኤርትራዊ የፖለቲካ ድርጅት አመራር ውስጥ ያለ ሰው እናት አገሬ ብሎ ኤርትራን ከመጥቀስ ይልቅ ባርካን ወይም ቢለንን ወይም ኩናማን ቢጠቅስ፡ ወይንም ደግሞ ከደጋማው አውራጃዎቻችን - ማለትም ሓማሴን፡ አከለጉዛይ - ብሎ ቢጠቅስ፡ ለኛ ለኤርትራውያን እጅግ የሚያሳስበን ይመስለኛል!!)

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የኢትዮጵያ ነገሥታት "እናት አገር" ሲሉ ሃሳቡ ኢትዮጵያን የሚያመላክት እየሆነ ነው የመጣው። ኢትዮጵያን' *"እናት አገር"* ብለው ነው የሚጠሯት! ለምሳሌ አጼ ዮሐንስ እንኳ፡ የተምቤን ተወላጅ የትግራይ ሰው ሆነው፡ ኢትዮጵያን ነበር እናት አገር የሚሏት። ይህንን በግልጽ የምታመለክት በብዙ የታሪክ ጸሓፍት ዘወትር የምትጠቀስ በጣም ጥልቅ ይዘት ያላት የኚህ አጼ ንግግር አለች። ንጉሡ በ1887 ዓ.ም ከጣሊያን ጋር ጦርነት ለመግጠም ወደ ሰሓጢ ዘመቻ ሲነሱ ለመኳንንቶቻቸውና

32. ዝኒ ከማሁ. ገጽ 168
33. ዝኒ ከማሁ፡ ገጽ 169

*ለሰራዊታቸው "እኔም ስለ እናቴ፡ ስለ ኢትዮጵያ ህይወቴን ልሰዋላት ሙሉ ፈቃድ ኣለኝ"* ካሉ በኋላ፡ የሚከተለውን አወጁ፤

> *"የኢትዮጵያ ልጅ ሆይ! ልብ አድርገህ ተመልከት! ኢትዮጵያ የተባለችው አንደኛ እናትህ ናት፤ ሁለተኛ ዘውድህ ናት፤ ሶስተኛ ሚስትህ ናት፤ አራተኛም ልጅህ ናት፤ አምስተኛም መቃብርህ ናት፡፡ እንግዲህ የእናት ፍቅር፤ የዘውድ ክብር፤ የሚስት ደግነት፤ የልጅ ደስታ፤ የመቃብር ካባቲነት (ታቃፊነት) እንደዚህ መሆኑን አውቀህ ተነሳ።"*[34]

ለአጼ ዮሃንስ እናት አገር ሲባል ኢትዮጵያ መሆኗ ግልጽ ነው። እንግዳውስ የትግራይ ፖለቲከኞች 'በዚህ ዘመን' እናት አገራችን 'ትግራይ' ነች ሲሉ የወደፊቷን ኢትዮጵያ በሚመለከት አመላካች ትርጉሙ ምንድነው? ወይም አሳሳቢነቱ ምን ያህል ነው? ይህ ሁኔታ ኤርትራንስ እንዴት ሊመለከታት ይችላል? የሚሉትን ጥያቄዎች ያስነሳል። ቢሆንም ጥያቄው ላሁኑ ወደ ጐን አስቀምጠን፡ የኤርትራን እናት-አገርነት የዕድገት (ወይም ጥንካሬ) መጠንና አይነት ወደሚመለከት ጉዳይ እናትኩር።

**- ፮-**

በታሪክ አይን ሲታይ ኤርትራዊ ብሔራዊ ማንነት ጥንታዊ አይደለም፣ ገና አፍላ ነው። ኤርትራ አገሬ ነች የሚል ስሜት በሰፊው ሕዝብ ማቆጥቆጥ የጀመረው በትግሉ ጉዞ ከነበረው መስዋዕትነት ስቃይና የብሔረሰቦች ግንኙነትና ትውውቅ ጋር በተያያዘ ነው። ለምሳሌ አንድ ኤርትራዊ አባት እናት አገርዎ ማን ናት ተብለው ሲጠየቁ *"ኤርትራ፤ ኤርትራ ነች እናት አገሬ! ሁለት ልጆቼ ለኤርትራ ነፃነት ታግለው፤ ስለ ኤርትራ መስዋእት ሆነዋል እኮ!"* አሉ።[35]

እንግዲያውስ ኤርትራ በመሰረቱ ብቻ ነው እንደ እናት አገር ያለችው። ከዚያ በተረፈ መጽናት፡ መብሰልና መጠናከር ያለባት ናት። በሌላ አነጋገር ኤርትራ እንደ እናት አገር ገና በሂደት ላይ ነች፤ መጠናቀቅ ያለባት ስራ ወይም ግብ (ፕሮጀክት) ነች።

እናት-አገርነት በንግግር ምሳሌዎች፤ ባህላዊ ምልክቶች፤ ተረቶች፤ አባባሎች የተሸገ የብዙ ግኝቶ ድምር መንፈስና ባህርይ ያለው ነው። የኤርትራ አገርነት እምቡጥ ስለሆነ እነኚህ ግኝቶችን በቂ በሆነ መጠን አላዳበረም። ስለሆነም የኤርትራ እናት-አገርነት (ዓደቦነት ኤርትራ) ብዙ ጥበቃ፤ ክንክንና ድጋፍ የሚያስፈልገው ነው። በሁሉም ዘርፎች -ማለትም በባህላዊ እንቅስቃሴዎች፡ በምጣኔ ሃብታዊ ዕድገት፡ በዜናና መረጃ ስርጭት፡ በብሔረሶቦቻችን ወንድማዊ እና እህትማማዊ ዝምድና፡ እንዲሁም ብቃትና ጠቃሜታ ባለው ስርአተ-ትምህርት፡ የኤርትራን እናት-አገርነት የሚያደምቅና የሚያጐለብት ጥንቁቅ በሆነ ጥናት ላይ የተሞረኰዘ ፖሊሲ ተነድፎ ስራ ላይ መዋል አለበት። ህፃናት እናት አገራቸው ኤርትራ መሆኗን በሚያመለክት ትምህርት መኰትኮት አለባቸው። ደራሲያን በጽሁፎቻቸው፡ የስነ-ጥበብ ሰዎች በተለያዩ የፈጠራ ስራዎቻቸው የኤርትራ እናት-አገርነትን እንደ ሃሳብ በሚያጐላና በሚደግፍ መልኩ ለመንቀሳቀስ እንዲፈቀድላቸውና እንዲበረታቱ ያስፈልጋል።

---

34. ተክለጻድቅ *መኩርያ*፡ ገጽ 471
35. ኣለምሰገድ ኣባይ (1998): ገጽ 170

*ታሪካችንን በትክክል መረዳት ለኤርትራ እናት-አገርነት ዕድገትና መጠናከር ማዕከላዊ አስፈላጊነት አለው። እንግዲህ ከገጠሙን አበይት ችግሮች አንዱ ይህ ነው። ኢሳያስ፡ የኢሳያስ ተባባሪዎችና ተላላኪዎች ከድሮ ጀምሮ የሕብረተሰባችንን የሩቅና የቅርብ ታሪክ ጠምዝዞ ተረት-ተረት የሚመስል ፈጠራ ለሰራዊታቸውና ለአባሎቻቸው፡ ለሕዝባችንና እንዲሁም ለመላ ዓለም ሳይታክቱ አሰራጭተዋል። በውሸት ታሪክ የታጠበው ሰራዊታቸውና ተከታዮቻቸው (በኤርትራ አብዮት ውስጥ) ለጸረ አንድነት ውግያ ታዛዥ ሆኖ ሳይታወቀው የኤርትራን አፈራርሶ 'ትግራይ-ትግርኚ'ን የመመስረት የኢሳያስ ግብ መገልገያ ሆነዋል።*

*እንግዲያውስ ሕዝባችን የእውነተኛ ታሪኩ ግንዛቤ እንዲኖረው መከናወን ያለባቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ግቡ እጅግ ውስብስብ ነው። እንዲህ የሆነበት ምክንያትም ሕዝቡ - በተለይ ወጣቱ - ትክክለኛ ታሪኩ ማወቅ ይኖርበታል ብቻ ሳይሆን በመጀመርያ ያ እስካሁን አውነተኛ የታሪክ ዕውቀት ብሎ የተቀበለው ውሸት ካስተሳሰቡ መደምሰስ ስለሚኖርበት ነው። ወጣቶቹ ያላቸው ታሪክን የሚመለከት ሐሳብ ስሕተተኛና ውሸት መሆኑን እንዲያምኑና እንዲቀበሉ መደረግ አለበት።*

*እንደሚመስለኝ፡ አንዳንዶቻችን ሓቀኛ ታሪካችንን ለማወቅ እንፈራለን። እውነተኛ ታሪካችንን ካወቅንና ካመንን ነፃነታችንና ሉዓላዊነታችን አደጋ ውስጥ የሚገባ ይመስለናል። ይህ ግን ከየዋህነት የመነጨ ፍርሃት ነው። በታሪክ ከመላ ጐረቤቶቻችን ጋር እንዛመዳለን። ይህንን እውነተኛ ታረክ መቀበል ነፃነታችንና ሉኡላዊነታችንን የሚጻረር አይደለም።*

*በምዕራባዊ ቆላ የሚኖሩት ሕዝቦቻችን በታሪክ ከምስራቃዊና ማእከላዊ ሱዳን ጋር ይዛመዳሉ። እንዳውም የጋራ ታሪክ ነው ያላቸው። ትግርኛ ተናጋሪው የደጋው ሕዝባችን ደግሞ በታሪኩ ከሰሜን ኢትዮጵያ ሕብረተሰቦች ጋር የሚዛመድ ነው። እንዲያውም የጣሊያን ቅኝ ግዛትነት እስከ ጀመረ ድረስ ወደ ኋላ ያለው ታሪክ ሁሉ የጋራ ታሪካችን ነው።*

*ታሪክ ሲባል ቀላል ነገር አይደለም። በዚህ ዘመን፡ በዚያ ዘመን እንዲህ ሆነላችሁ እያለ የፍጻሜ ድርጊቶች የሚያወሳ አፈ ታሪክ ወይም ተረት ብቻ አይደለም። ታሪክ በአንድ ሕዝብ አካሄድ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድር ብቻ ሳይሆን፡ የአካሄዱን ቅርጽ የሚሰጥ፡ የአንድን ሕዝብ የሥልጣኔ ሂደት አቅጣጫ የሚያስይዝ፡ የማንነት ስሜትን፡ ባህልን፡ ሃይማኖትን፡ ቋንቋን፡ ወግንና ክብረትን (ወይም ጨዋነትን) ሁሉ ያቀፈ፡ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ በቅርስ መልክ የሚኖር ህያው ነገር ነው። እውነተኛ ታሪኩን የሚክድ ሕዝብ የማንነት ቀውስ አጥቅቶት፡ በተምታታ ባህል እየተደናበረ በመዳከር ላይ ገብቶ ወንድሞቹ በሆኑት በጐረቤት ሕብረተሰቦች ላይ የተሳሳተ አፍራሽ እይታ ሊኖሮው የግድ ነው።*

*ታሪክን በሚመለከት እንግዲህ እኛ ኤርትራውያን ልንገነዘበው የሚገባን አሳሳቢ ነጥብ አለ። የምስራቃዊና ማእከላዊ ሱዳን ታሪክ በውንድሞቻችን በኒ-ዓምር እና በሌሎቹ የምዕራባዊ ቆላ ሕብረተሰቦቻችን በኩል ይደርሰናል። የኢትዮጵያ ታሪክም ቢያንስ በትግርኛ ተናጋሪው የደጋው ሕብረተስብ አድርጐ ይደርሰናል። ይህንን ታሪክ ማወቅ አለብን ብቻ ሳይሆን፡ አሁን ላሉን የሃይማኖት፡ የባህል፡ የወግ፡ የማዕረግና የስነምግባር ሕጐችን ቅርጽ ያስያዘ - ባጭሩ ጠቅላላ ማንነታችን የገነባ - መሆኑን በማመን የኛ የራሳችን ነው ብለን መቀበል ይገባናል። ታሪካችንን ማወቅ፡ ደካማና አሉታዊ ጐኖቹን ለይተን እንድንጠነቀቅባቸው፤ ገምቢና አዎንታዊ ጐኑንም ልናከብረው፡ ልንኰራበትና ልንንከባከበው እጅግ አስፈላጊ ነው። እንዲህ ስናደርግ ብቻ ነው፡ በአካሄዳችን በአላማችንና በአመለካከታችን ኤርትራ እናት አገራችን መሆኗን በተግባር ልናስመሰክር የምንችለው።*

## - ፯ -

*አስቀድሜ እንደጠቀስኩት የኤርትራ እናት-አገርነት በ40ዎቹ በትግራይ-ትግርኚ መርሆ ፈተና ውስጥ ነበር። እንዲያውም በዚህ መርሆ መሰረት የተጠየቀው ተሟልቶ ትግራይና ኤርትራ አንድ አገር ቢሆኑ ኖሮ፡ በቁጥር እኩል የሆኑት እስላሞችና ክርስትያኖች የሚኖሩባት ኤርትራ ዞራ ዞራ መበታተኗ አይቀርም ነበር። ለምን? ትግራይ-ትግርኚ ተብሎ ሊቆም በታሰበው አገር፡ ያ ክርስትያናዊ አካል ከእስላሙ ክፍል በቁጥር የበላይነት ስለሚኖሮው፡ የብዛተ-ህዝብ ሚዛን (ደሞግራፊክ ባላንስ) በደፈረሰ ነበር። እንዲያ ሲሆን፡ እንዳልጨፈለቅ በሚል ስጋት ምዕራባዊ ቆላ ውስጥ የሚኖሮው ህዝባችን ወደ ሱዳን መጠቃለል ይሻለናል በማለት እንቅስቃሴ መፍጠሩ አይቀርም ነበር። እንግሊዞቹም ያ ነበር ዕቅዳቸው።*

*የሆኖ ሆኖ የትግራይ-ትግርኚ ንድፈ ሃሳብ ግቡን አልመታም። አባቶቻችን አገር እንዳትገነጣጠል በማሰብ፡ ፈደረሽንን እንደ ማእከላዊ መፍትሔ ተቀብለው የኤርትራ አንድነት እንዲረጋገጥ አደረጉ። እንግዳውስ ያ ፈደረሽን የኤርትራ እናት-አገርነት መሠረት እንዲቀጥል አስተዋጽኦ አድርጓል ማለት ይቻላል።*

*ዛሬም የኤርትራ እናት-አገርነት በአንዲት መጥፎና አስጊ የሆነች መፈክር እየተፈተነ ወይም ለአደጋ እየተጋለጠ ነው። ያች መፈክርም አስቀድሜ የጠቀስኩዋት **"የብሔሮች መብት እስከ መገንጠል"** የምትለዋ ናት። ይህች መፈክር ብላ-ብላ ከላይ ከተመለከተው ከእነ አቶ ስብሃት ነጋና አቶ ጸጋይ በርሀ አስተሳሰብ ጋር ነው የምትያያዘው። እነዚህ ሁለት የወያኔ መሪዎች "እናት አገራችን ትግራይ ናት" (ኢትዮጵያ ሳትሆን ትግራይ ናት) እንዳሉት ሁሉ፡ አንዳንድ የብሔሮች መብት አስጠባቂዎች ነን የሚሉት ፖለቲከኞቻችንም እናት አገራችን ኤርትራ ሳትሆን ከብሔሮቻችን አንድዋ (ለምሳሌ "ኩናማ፡ ብሌን፡ ትግረ ወይም ከደጋው አውራጃዎቻችን አንድዋ ለምሳሌ አከለ-ጉዛይ ወይንም ሐማሴን) ናት ሊሉ ነው ማለት ነው። ይህ አቋም የኤርትራን እናት-አገርነት ያለ ምሕረት የሚፈታተን ነው።*

*ለኤርትራ የመሬት ወይም የግዛት ሙሉነትና እናት-አገርነት ቆሞ መከላከል ትግራይን ማስወገድ አይደለም፣ እንደዚያ ተብሎም መተርጎም የለበትም። ይህችን ነጥብ ላሰምርባት እፈልጋለሁ። ኤርትራና ኢትዮጵያ ሁለት የተለያዩ፡ የየራሳቸው ሉዓላዊነት ያላቸው አገሮች እንኳ ቢሆኑም በሁለቱ መካከል በሁሉም መስኮች ወንድማዊ ዝምድናዎች የማይኖሩበትና የማያድጉበት ምክንያት የለም። ኤርትራና ትግራይማ በቀጥታ በድምበር የሚገናኙ ስለሆኑ ዝምድናቸው የጐላ ነው። በተለይ ደግሞ በድምበር አካባቢ ያሉት የኤርትራ እና የትግራይ ማሕበረሰቦች ለዘመናት ሲቀላቀሉና ሲዋሃዱ የነበሩ ናቸው። እንዲያውም ለነዚህ ሕዝቦች የድምበሩ መስመር ተግባራዊ ወይም እውነተኛ ትርጉም የለውም፡ አይታያቸውምም። ስለዚህ ከትግራይ ሕዝብ ጋር የነበረ ጥንታዊ ዝምድናችን እንዳይቀጥል የሚያግደው አንዳችም ነገር የለም።*

*ኢትዮጵያዊያን የትግራይ ወንድሞቻችን ይህችን የብሄሮች መብትንና የኤርትራን አንድነት ጉዳይ የምትመለከተውን አስተያየቴ፡ በዛው ባቀረብኳት የወዳጅነትና የሰላም መንፈስ እንዲያጣጥሟት ለማሳሰብ እሻለሁ።*

*ለኤርትራ እናት-አገርነት ገጥሞት የሚገኝ አስገራሚ ችግርና ከባድ ፈተና ባጭሩ ከዳሰስኩ በኋላ የተማጽኖ መንፈስ ባዘለ ቃና መልዕክቴን በማስተላለፍ ሃሳቤን እደመድማለሁ።*

በመከፊቻ ንግግሬ እንዳስቀመጥኩት ዛሬ ኢትዮጵያ በድህረ-መለስ ዘመን ውስጥ ትገኛለች። አገርን በመምራት ትልቅ ሚናና ተሰሚነት ወይም ተጽዕኖ የነበረው ሰው በሞት መለየት አንድ አሰሳቢ ምዕራፍ ነው። አሳሳቢ የሚሆንበት ምክንያትም የሚያስከትላቸው ነገሮች ወይም አደጋዎች ስላሉ ወይም ሊኖሩ ስለሚችሉ ነው።

ሕዝባዊ ወያኔ ከበረሃ ትግል ወቅት ጀምሮ እስካሁኗ ደቂቃ ድረስ ኤርትራን በሚመለከት ጉዳይ ትልቅ ሚና ነበራቸው፥ ዛሬም ቢሆን ገና አላቸው። በመለስ ዜናዊ አመራር የተከተሉት ስትራተጂና መላ አምባገነኑን ኢሳያስ እና ወደር የሌለው አራዊታዊ ስርዓቱን በመሰረቱ ጠቅሞታል እንጂ አልጐዳውም። የኤርትራን ሕዝብ ግን በእርግጥ ጐዳው፣ አገራችን የምድር ገሃነብ እንድትሆን አስተዋጽኦ አድርጓል።

አቶ መለስ እንደ ግለሰብ የሚደነቅ ችሎታ እንደነበረው ብዙ ታዛቢዎች የሚመሰክሩት ነው። እኔም በብቃቱና በብርታቱ እጅግ ከሚያደንቁት አንዱ ነኝ። ኤርትራን በሚመለከት በተከተለው ፖሊሲ ግን ድሮ አላመሰገንኩትም፣ አሁንም አላመሰግነውም። አሁን-አሁን ሟቹ መለስ የፖሊሲ ለውጥ ለማድረግ ዕቅድ ነበረው፣ ሊተገበረውም ጀምሮ ነበር የሚል ነገር ይሰማል። ሊተገበር የታሰበው ለውጥ - እውነት ከሆነ - እዚህ መልእክት ሠፍረው ያሉትን ጉዳዮች ምን ያህል ሊመለከታቸው ይችል እንደነበር የማረጋግጥበት መንገድ ባሁኑ ጊዜ የለኝም።

የሆኖ ሆኖ አሁን አዲስ ሁኔታ ተከስቷል። ይህ ሁኔታ ደግሞ ለሕዝባዊ ወያኔ አመራሮች በአካሂዳቸው ለውጥ እንዲያደርጉ በር ከፍቶላቸዋል። ያለፈው አካሄዳቸውን ያለምንም ማወላወል ገምግመው የኤርትራ ሕዘብ አሁን ላለበት አዘቅት እንዲዳረግ እነርሱም በምን መልኩ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ በጥሞና (ከልብ) መመራመር አለባቸው። ከዚህ ተነስተው የኤርትራ አንድነት፥ ሉኡላዊነትና እናት-አገርነት እንዲጐለብት፥ የኤርትራና ኢትዮጵያ መልካም ዝምድና ደግሞ እንዲጠነክርና እንዲያድግ የሚያስፈልጉ ጥገናዎች እንዲያደርጉ እማጠናለሁ።

---

## **ማጣቀሻ** (Bibliography)

Alemseged Abbay, *Identity Jilted or Re-Imagining Ide?*, (Lawrenceville, NJ: The Red Sea Press, 1998)

Alemseged Abbay, "The Trans-Mereb Past in the Present", *The Journal of Contemporary African Studies*, vol. 35, No. 2, (1997)

Amare Tekle, "*The Creation of the Ethio-Eritrean Federation: A Case Study in the Post War International Relations (1945-1950),"* PhD dissertation, University of Denver, 1964.

Haggai Erlich, "Tigrean Nationalism, British Involvement and Haile-Sellasse's Emerging Absolutism – Northern Ethiopia, 1941-1943", *Asian and African Studies*, Vol. 15 (1982)

Richard Greenfield, "Pre-colonial and Colonial History", in Basil Davidson, Lionel Cliffe, and Bereket Habte Selassie, *Behind the War in Eritrea,* (Notingham: The Spokesman Press 1980)

Rene Lefort, *Ethiopia: An Heretical Revolution?* (London: Zed Press, 1983)

Medhane Tadesse, *The Eritrean-Ethiopian war: Retrospect and Prospects*, (Addis Ababa: Mega Printing Enterprise, 1999)

John Spencer, *Ethiopia*, *The Horn of Africa and US Policy* (Cambridge, Mass.: Institute for Foreign Policy Analysis, 1977)

Tekeste Negash, *Italian Colonialism in Eritrea, 1882-1941: Policies, Praxis and Impact,* (Uppsala: Acta Universitatis Upsaliens, 1987)

US Congress, Sub Committee on African Affairs, *Ethiopia and the Horn of Africa*, *Hearings*, 94th Congress, 2nd Session, Aug. 4, 5, and 6, 1976.(Washington, D. C.)

Maurizio Viroli, *Republicanism*, (New York: Hill and Wang, 1999)

**ኣለምሰገድ ተስፋይ፤** ***ኣይንፈላለ 1941-1950*** (**ኣስመራ፤ ሕድሪ፡** 2001)

**ረድኢ መሓሪ፤** ***ትልሚ ንዘርኢ ክርዳድ፤*** (**ኪቾነር፡ ኦንታርዮ፤ ኣለና፡** 2012)

**ተክለ ጻድቅ መኩርያ፤** ***ዐፄ ዮሃንስ እና የኢትዮጵያ ኣንድነት*** (**ኣዲሰ-አበባ፤ ኩራዝ ኣሳታሚ ድርጅት፡** 1982)

Copyright © 2012 by Tesfatsion Medhanie.
**የደራሲው መብት** © 2012 **ተስፋጽዮን መድሃኔ፡፡**